የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት
THE FEDERAL DEMOCRATIC
REPUBLIC OF ETHIOPIA
OFFICE OF THE FEDERAL
AUDITOR GENERAL

ቁጥር OFAG.P-01.2/1
ቀን 16/08/ 2015

ለአቶ ፉፌሳ ሽጋ ቡራቃ
የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ገቢ ማመንጫ ኢንተርፕራይዝ
ዋና ሥራ አስኪያጅ
<u>ሀዋሳ</u>

መ/ቤታችን በአዋጅ በተሰጠው ሥልጣንና ኃላፊነት የፋይናንሻልና ህጋዊነት እንዲሁም የክዋኔ ኦዲት የሚያከናውን መሆኑ ይታወቃል፡፡

በዚሁ መሠረት መ/ቤታችን በሀዋሳ ዩኒቨርስቲ የገቢ ማመንጫ ኢንተርፕራይዝ እና የስጦ ገቢ ማመንጫ (ሪሶርስ ሞባላይዜሽን) የስራ አፈጻጸም ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋና ጤታማ መሆኑን በተመለከተ የአሠራር ችግሮች ካሉ ችግሮቹን ለይቶ በማውጣት ችግሮቹን ለማስወገድ ወይም ለመቀነስ የሚያስችሉ የማሻሻያ ሀሳቦችን ለመስጠት የክዋኔ ኦዲት ማካሄዱ ይታወሳል፡፡

በዚሁ መሠረት ለክዋኔ ኦዲቱ የሚጠቅሙ ማስረጃዎች ከኢንተርፕራዙና ማዕከላት እንዲሁም ከዩኒቨርሲቲው ኮሌጆች ተሰብስበው ከተገመገሙ በኋላ ኦዲቱ ተጠናቆ የተገኘውን ውጤትና የተሰጠውን የማሻሻያ ሀሳብ የያዘ ረቂቅ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት በደብዳቤ ቁጥር OFAG.P-01.22/1/6 በቀን 30/06/2015 ዓ.ም መላካችን ይታወሳል፡፡

በመሆኑም በተላከላችሁ ረቂቅ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት ላይ ያላችሁን አስተያየት የገለጻችሁና በመውጫ ስብሰባ ወቅት በኦዲት ግኝቶቹ ላይ የተደረገውን ውይይት ከግንዛቤ ውስጥ ያስገባ <u>45</u> ገጽ ሪፖርት እና <u>10</u> ገጽ አባሪ በድምሩ <u>55</u> ገጽ የመጨረሻ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት ከዚህ ደብዳቤ ጋር አያይዘን የላክን ሲሆን በመ/ቤታችን የማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 982/2008 ዓ.ም መሰረት ሪፖርቱን በዓመታዊ ሪፖርታችን ውስጥ በማካተት ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የምናቀርብ መሆኑን እንገልጻለን፡፡

በተጨማሪም በተላከላችሁ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት ውስጥ በኦዲት ወቅት የተገኙ ዋና ዋና የአሰራር ክፍተቶችንና ድክመቶችን አስመልክቶ የማስተካከያ እርምጃዎችን በመውሰድ አሰራሩን ሕግን የተከተለ ግልጽ እና ውጤታማ ማድረግ ይጠበቅባችኋል፡፡

ስለዚህ ለክትትል ያመቸን ዘንድ መ/ቤታችሁን በተመለከተ በተደረገው የክዋኔ ኦዲት ወቅት የተሰጣችሁን የማሻሻያ ሀሳቦች ተግባራዊ የምታደርጉበትን መርሀ ግብር ከዚህ ደብዳቤ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ መሠረት ነድፋችሁ በአስራ አምስት የስራ ቀናት እንድታሣውቁን እናሣስባለን፡፡

ከሰላምታ ጋር

ጳውሎስ ዘሪሁን እታለል
የልማትና ማህበራዊ አገልግሎቶች
ክዋኔ ኦዲት ዳይሬክቶሬት
ዳይሬክተር

<u>ግልባጭ፣</u>

- ለክብርት አምባሳደር ናሲሳ ጫሊ
  የቱሪዝም ሚኒስትርና
  የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ቦርድ ሰብሳቢ
- ለክቡር ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ
  የትምህርት ሚኒስትር
  <u>አዲስ አበባ</u>
- ለዶ/ር አያኖ በራሶ
  የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዝዳንት
  <u>ሀዋሳ</u>

በክዋኔ ሪፖርት በተጠቀሱት የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሀሣቦች አተገባበር መርሐ-ግብር

የኦዲት ተደራጊ መ/ቤት ስም የሀዋሳ ዩኒቨርስቲ የገቢ ማመንጫ ኢንተርፕራይዝ

የክዋኔ ኦዲቱ አርዕስት ____________________

መርሃ-ግብሩ የተዘጋጀበት ቀን ____________________

ተ.ቁ.	የኦዲት ግኝቶች	የተሰጡ ማሻሻያ ሃሣቦች	እስከአሁን የተወሰዱ የማስተካከያ እርምጃዎች	ቀሪ ማሻሻያ ሃሣቦች ተግባራዊ የሚደረጉበት ጊዜ	ኃላፊነት የተሰጠው የሥራ ክፍል	ምርመራ

ማሳሰቢያ፡- ይህን መርዓ-ግብር እና የተወሰዱ እርምጃዎች የኦዲት ሪፖርቱ ለመ/ቤትዎ እንደደረሰ በ15 ቀናት ውስጥ ተሞልቶ ለመ/ቤታችን ካልተመለሰ ለሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት በምናቀርበው ዓመታዊ ሪፖርት ውስጥ "ለኦዲት ሪፖርት ማሻሻያ ሀሣቦች አተገባበር መርዓ -ግብር መልስ ያልላኩ መ/ቤቶች" ዝርዝር ውስጥ እና በማሻሻያ ሀሳቡ መሰረት እርምጃ አለመወሰዱ ተጠቅሶ ለም/ቤቱ ሪፖርት የሚቀርብ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

በሀዋሳ ዩኒቨርስቲ የገቢ ማመንጫ ኢንተርፕራይዝ እና የውስጥ ገቢ ማመንጫ (ሪሶርስ ሞባላይዜሽን) የስራ አፈጻጸም ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ መሆኑን በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት

ሚያዚያ 2015 ዓ.ም

አዲስ አበባ

ማጫ

ማጫ i
የክዋኔ ኦዲቱ ማጠቃለያ (Executive summary) I
ክፍል አንድ 1
መግቢያ 1
የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ የገቢ ማመንጫ ኢንተርፕራይዝ አመሰራረት..2
የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ የገቢ ማመንጫ ኢንተርፕራይዝ ተልዕኮ ራዕይ እና ዓላማ፡-................................3
የኢንተርፕራይዙ ተልዕኮ፡- 3
የኢንተርፕራይዙ ራዕይ፡-...3
የኢንተርፕራይዙ ዓላማ፡- 3
የኢንተርፕራይዙ የንግድ ስራ ዓላማዎች፡- 3
የመንግስት ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ተግባርና ኃላፊነት..4
የኢንተርፕራይዙ ቦርድ ተግባርና ኃላፊነት 4
የኢንተርፕራይዙ ዋና ስራ አስኪያጅ ተግባርና ኃላፊነት 5
የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ገቢ ማመንጫ ኢንተርፕራይዝ ድርጅታዊ መዋቅር እና የሰው ኃይል አደረጃጀት..............6
የኢንተርፕራይዙ ድርጅታዊ መዋቅር...6
የኢንተርፕራይዙ የሰው ኃይል አደረጃጀት...6
የኢንተርፕራይዙ የፋይናንስ ምንጮ...6
የኦዲቱ ዓላማ...7
የኦዲት አካባቢ (Audit Area)...8
የኦዲት ትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issues)..8
የኦዲት መመዘኛ መስፈርት (Audit Evaluative Criteria 8
የኦዲት ወሰንና ዘዴ...9
የኦዲቱ ወሰን..9
የኦዲቱ ዘዴ 9
ክፍል ሁለት 10

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት

ግኝቶች 10

2.1 የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ የገቢ ማመንጫ አስተዳደር እና አሰራር የሀገሪቱን ህግና ስርዓትን የተከተለ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ መሆኑን መገምገም፤....10

የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ የገቢ ማመንጫ ኢንተርፕራይዝ ተጠሪነትን በተመለከተ፡-....10

የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ የገቢ ማመንጫ ኢንተርፕራይዝ ካፒታል በተመለከተ፤....11

የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ የገቢ ማመንጫ ኢንተርፕራይዝ ከሚያገኘው ትርፍ ላይ ለዩኒቨርሲቲው ተልዕኮና አላማ ማስፈጸሚያ ያዋለ መሆኑን በተመለከተ፡-....13

ኢንተርፕራይዙ በየአመቱ ሂሳቡን እየዘጋ ኦዲት ማስደረጉን በተመለከተ፤....14

ኢንተርፕራይዙ በሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ያሉ ባለሙያዎችን ለመጠቀም ግልጽ የሆነ መስፈርት አውጥቶ ተግባራዊ ማድረጉን በተመለከተ፡-....16

የኢንተርፕራይዙን የአገልግሎት አሰጣጥ ቅሬታዎች የሚስተናገዱበት ስርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ፤ 20

የኢንተርፕራይዙ የስራ ፕሮግራምና፣ በጀት በቦርድ መጽደቁን እና በየጊዜ አፈጻጸሙ መገምገሙን በተመለከተ፤....21

2.2 የገቢ ማመንጫ ኢንተርፕራይዙ የገቢ ማመንጫ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የተዘረጋ ሥርዓት ኢኮኖሚያዊ ፣ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መልኩ ማሳደጉን መገምገም፣....22

የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ገቢ ማመንጫ ኢንተርፕራይዝ የግዥ እቅድ አዘጋጅቶ በቦርድ ያጸደቀ መሆኑን በተመለከተ፤....22

በኢንተርፕራይዙ ለሚቀርቡ አገልግሎቶች እና ምርቶች ክፍያዎች በወቅቱ መሰብሰባቸውን በተመለከተ፤ ..23

ኢንተርፕራይዙ የውስጥ ኦዲት ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረጉን በተመለከተ፡-....26

ኢንተርፕራይዙ በስሩ ላሉ የስራ ክፍሎች ስልጠና መስጠቱን በተመለከተ፤....26

ኢንተርፕራይዙ የገቢ ማመንጫ ዘርፎችን ማስፋፋቱን እና ማጠናከሩን በተመለከተ፤....27

2.3 የገቢ ማመንጫ ኢንተርፕራይዙ የሀብት አስተዳደር፣ የገበያ ጥናት እና መረጃ አያያዝና ልውውጥ ስርዓት በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ መሆኑን መገምገም፤....30

ኢንተርፕራይዙ አዳዲስ ለሚከፍታቸው ገቢ ማመንጫ የአዋጭነት ጥናት ማድረጉን እና በቦርድ እንዲወሰን መደረጉን በተመለከተ፤....30

ኢንተርፕራይዙ አገልግሎቶቹን እና ምርቶቹን የሚያስተዋቅበት ስርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ፡-....31

የስራ አመራር ቦርዱ የኢንተርፕራይዙን አፈጻጸም ክትትል እና ግምገማ ማድረጉን በተመለከተ....32

ኢንተርፕራይዙ የግምገማ ስርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ....33

የኢንተርፕራይዙ የመረጃ አያያዝና ልውውጥ ስርዓትን በተመለከተ....33

ኢንተርፕራይዙ የሚጠቀምባቸው ማሽኖች ሲበላሹ አፋጣኝ ጥገና ማድረጉን በተመለከተ፤......................34

ኢንተርፕራይዙ ተገቢን መረጃ ለሚመለከተው አካል ማሳወቁን በተመለከተ፤.......................................35

የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ከሚሰጠው አገልግሎት ጋር ተያያዥ የሆኑ ገቢ ሊያስገኙ የሚችሉ አገልግሎቶች በዩኒቨርሲቲው የገቢ ማመንጫ ኢንትርፕራይዝ ሥር መደራጀታቸውን በተመለከተ፡-............................36

ክፍል ሦስት..38

መደምደሚያ...38

ክፍል አራት..40

የማሻሻያ ሃሳቦች..40

አባሪ፡ 1 የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ገቢ ማመንጫ ኢንተርፕራይዝ ኃላ/የተ/የግ/ማህበር ድርጅታዊ መዋቅር.........43

አባሪ 2 ፡- የመመዘኛ መስፈርት (Evaluative Criteria)..44

አባሪ፡- 3 በዩኒቨርስቲው የማማከር አገልግሎት ማህበር የተሰሩ ስራዎች 48

አባሪ 4፡- በዝርዝር ኦዲት ወቅት የተከለሱ መረጃዎች 51

አባሪ፡ 5 በኦዲት ወቅት በናሙና ተመርጠው የታዩ የኢንተርፕራይዙ ማዕከላት እና የዩኒቨርስቲው ኮሌጆች..52

የክዋኔ ኦዲቱ ማጠቃለያ (Executive summary)

መንግስት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ከመንግስት የሚበጅትላቸውን በጀት ለመደጎም እንዲሁም ከውስጥ ገቢያቸው እራሳቸውን ችለው ለመቋቋም የሚያደርጉትን ጥረት ለመደገፍ የሚያስችል የገቢ ማመንጫ ድርጅት ማቋቋም እንደሚችሉ በከፍተኛ ትምህርት መቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 66 እና በተሻሻለ የከፍተኛ ትምህርት መቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 1152/2011 ዓ.ም አንቀጽ 64 እንዲሁም በከፍተኛ ትምህርት የገቢ ማስገኛ ድርጅቶች ማቋቋሚያ ደንብ 456/2012 ዓ.ም ደንግጓል፡፡

በዚሁ መሰረት የሀዋሳ ዩኒቨርስቲ የገቢ ማመንጫ ኢንተርፕራዝ በ2007 ዓ.ም ተቋቁሞ በስሩ በተደራጁ ማዕከላት የሚመረቱ ምርቶች እያመረተ እና አገልግሎቶች እየሰጠ ይገኛል፡፡

የክዋኔ ኦዲቱ አላማ በሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ የገቢ ማስገኛ ኢንተርፕራይዝ እና የውስጥ ገቢ ማመንጫ (ሪሶርስ ሞባላይዜሽን) አፈጻጸም ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ መሆኑን መገምገም የሚል ሲሆን ከዚሁ ጋር በተያያዘ የአሰራር ክፍተቶችን በመለየት ችግሮቹን ለመቅረፍ ወይም ለማቃለል የሚረዱ የማሻሻያ ሃሳቦችን ለመስጠት ነው፡፡

ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጡት የትኩረት አቅጣጫዎች፤

I. የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ የገቢ ማመንጫ አስተዳደር እና አሰራር የሀገሪቱን ህግና ስርዓትን የተከተለ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ መሆኑን መገምገም፤
II. የገቢ ማመንጫ ኢንተርፕራይዙ የገቢ ማመንጫ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የተዘረጋ ሥርዓት ኢኮኖሚያዊ ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መልኩ መከናወኑን መገምገም፣
III. የገቢ ማመንጫ ኢንተርፕራይዙ የሀብት አስተዳደር፣ የገቢያ ጥናት እና መረጃ አያያዝና ልውውጥ ስርዓት በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ መሆኑን መገምገም፣

የሚሉ ናቸው፡፡

ኦዲቱ የተከናወነው በሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ የገቢ ማመንጫ በዋና መ/ቤት፣ በናሙና በተመረጡ የኢንተርፕራይዙ ማዕከላት እና የዩኒቨርሲቲ ኮሌጆች ማስረጃዎችን በመከለስ፣ ለሚመለከታቸው የስራ ሀላፊዎች ቃለ መጠይቅ በማድረግ፣ መረጃዎችን በመተንተን እና በአካል ምልከታ በማድረግ ነው፡፡

ኦዲቱ የተከናወነው በአለም ዓቀፍ የዋና ኦዲተር መ/ቤቶች የክዋኔ ኦዲት ደረጃዎች (International Standards of Superem Audit Institutions (ISSAI) እና በመንግስት መ/ቤቶች እና ድርጅቶች ላይ የክዋኔ ኦዲት ለማድረግ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በተሰጠው አዋጅ ቁጥር 982/2008 መሠረት ሲሆን በኦዲቱ ወቅት የተገኙትን ዋና ዋና ግኝቶች እንደሚከተለው ቀርቧል፡-

- የሀዋሳ ዩኒቨርስቲ የገቢ ማስገኛ ኢንተርፕራይዝ በ2007 ዓ.ም ተጠሪነቱ ለዩኒቨርስቲው ፕሬዚዳንት ሆኖ የተቋቋመ ሲሆን አዲስ በወጣ የገቢ ማስገኛ ድርጅቶች ደንብ ቁጥር 456/2012 አንቀፅ 5 ንኡስ አንቀፅ 1 እና አንቀፅ 6 ንኡስ አንቀፅ 1 መሰረት እንዲሁም በመመሪያ 04/2012 ዓ.ም አንቀጽ 7(1) እንደገና ዩኒቨርሲቲውን ለሚያስተዳድር ቦርድ ተጠሪ ሆኖ ያልተቋቋመ መሆኑ፤
- የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ የገቢ ማመንጫ ኢንተርፕራይዝ በ2007 ዓ.ም ሲቋቋም በጥሬ ገንዘብ ከተከፈለ ካፒታል በተጨማሪ ከዩኒቨርሲቲው በአይነት የተሰጡት የገቢ ማስገኛ ማዕከላት ንብረቶች በባለሙያ በትክክል ተገምቶና በኦዲተር ተረጋግጦ በወቅቱ በነበረው የገበያ የዋጋ ተመን መሰረት ምን ያህል ዋጋ እንዳላቸው በትክክል ታውቀ ወደ ኢንተርፕራይዙ ካፒታል ውስጥ ያልተካተቱ መሆኑን፣
- ድርጅቱ ከሚያገኘው የተጣራ ትርፍ በህጉ መሰረት 80 በመቶን ለዩኒቨርስቲው ተልዕኮና አላማ ማስፈጸሚያ ያላዋለ መሆኑ፤
- ኢንተርፕራይዙ በሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ያሉ ባለሙያዎችን በማማከር አገልግሎት ላይ የሚጠቀም ሲሆን በጊዜያዊነት እንዴት እንደሚጠቀምባቸው ግልጽ የሆነ መስፈርት የሌለ መሆኑ፣ በተጨማሪም ኢንተርፕራይዙ ሲጠቀም የዩኒቨርሲቲ ባለሞያዎችን ሲጠቀም ባለሙያዎቹ ላቋቋሙት ህጋዊ ሰውነት ለሌላቸው ማህበራት ኮንትራት እየሰጠ መሆኑ እንዲሁም የክፍያ አተማመን ህጋዊ የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ያላደረገ መሆኑ፤
- ኢንተርፕራይዙ ለሰጣቸው አገልግሎቶች ያልሰበሰባቸው ተሰብሳቢ ሂሳቦች መኖራቸው፣ የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ከኢንተርፕራይዙ መንቀሳቀሻ ካፒታል ላይ ብር 35,075,000 ወጪ ተደርጎ ለአዲስ አበባ እንግዳ ማረፊያ ቤት ግዥ የዋለ ሲሆን ገንዘቡ እንዲመለስ አለመደረጉ፤
- ኢንተርፕራይዙ ከ2012 ዓ.ም ጀምሮ ዓመታዊ ሂሳቡን መመሪያው በሚጠይቀው በአይኤፍ አርኤስ (IFRS) የፋይናንስ አመዘጋገብ ስርዓት መሰረት ሂሳቡን

የማይዘጋ መሆኑን እንዲሁም በየአመቱ የሂሳብ መግለጫውን ትክክለኛነት በዋና ኦዲተር ወይም ዋና ኦዲተር በሚሰይም አካል ኦዲት እየተደረገ የሚይረጋገጥ መሆኑን

- የሀዋሳ ዩኒቨርሰቲን በበላይነት የሚያስተዳድረው ቦርድ በየሶስት ወር እየተሰበሰበ የኢንተርፕራይዙን አፈጻጸም የሚይገመግም እንዲሁም የኢንተርፕራይዙን ስራዎች በቅርበት የሚከታተል እና የሚደግፍ ኮሚቴ አቋቁሞ ቁጥጥር የማያደርግ መሆኑ፤
- የኢንተርፕራይዙ የመረጃ አደረጃጀት፣ አያያዝ እና ልውውጥ ስርዓት በዘመናዊ ኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ ስርዓት ያልተደገፈ መሆኑ፤

የሚሉ ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ፤ የተጠቀሱትን የኦዲት ግኝቶች ለማሻሻል የሚረዱ የማሻሻያ ሀሳቦች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

- የሀዋሳ ዩኒቨርስቲ የሥራ አመራር ቦርድ የገቢ ማመንጫ ኢንተርፕራይዙ የረጅም የመካከለኛ እና አመታዊ የስራ ዕቅዱን ለማስፈጸሚያ የሚያስፈልግን በጀት ማዘጋጀቱን እና ከዩኒቨርሲቲው ተልዕኮ ጋር የተጣጣመ መሆኑን ቢያንስ በየሦስት ወሩ እየተሰበሰበ በመገምገም ሊያጸድቅ እና አፈጻጸሙንም በየጊዜው መገምገም አለበት፡፡ ኢንተርፕራይዙ ለአመቱ ሥራ የሚያስፈልገን የግዥ ዕቅድ ፍላጎት በማዘጋጀትና ለሥራ አመራር ቦርድ በማቅረብ እና በማጸደቅ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ የገቢ ማመንጫ ኢንተርፕራይዝ ሲቋቋም ከዩኒቨርሲቲ በአይነት የተሰጠ ሀብት ግምት በባለሙያ ተገምቶ እና በኦዲተር ተረጋግጦ የኢንተርፕራይዙ ካፒታል ውስጥ እንዲካተት ሊያደርግ ይገባል፣ ተግባራዊነቱንም የሥራ አመራር ቦርዱ ሊከታተል ይገባል፡፡
- ኢንተርፕራይዙና የሥራ አመራር ቦርዱ በየአመቱ በIFRS መሰረት የሂሳብ መግለጫዎቹን በማዘጋጀት ኦዲት ያልተደረጉትን አመታት የሂሳብ መግለጫዎችን ጭምር በፌዴራል ዋና ኦዲተር ወይም እርሱ በሚሰይመው የኦዲት ተቋም ኦዲት ማስደረግ ይጠብቅበታል፡፡ በተቋሙ የሂሳብ መግለጫዎች ላይ የሚታዩ ተሰብሳቢ ገንዘቦችን ለዩኒቨርሲቲ የእንግዳ ማረፊያ የተሰጠን ብር 35,075,000 ጨምሮ ትኩረት ሰጥቶ ሊሰበስብ፣ የማይሰበሰቡ ሂሳቦችም ካሉ ምክንያታቸው ተጣርቶ በህግ መሰረት ከሂሳብ መዝገብ እንዲሰረዙ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡ በተጨማሪም ኢንተርፕራይዙ ከሚያገኘው የተጣራ ትርፍ ላይ 80 በመቶን ለዩኒቨርሲቲው ተልዕኮና አላማ ማስፈጸሚያ በህጉ መሰረት ማዋል ይኖርበታል፡፡ የሥራ አመራር

ቦርዱም ይህ መደረጉን በዩኒቨርሲቲው በጀት ውስጥ መካተቱን ማረጋገጥ ይጠበቅበታል፡፡

- ኢንተርፕራይዙ የንግድ ፈቃድ የወጣባቸውን የማማከርም፣ የጥናት እና ሌሎች ተዛማች ሥራዎች ለማሰራት የዩኒቨርሲቲን አካዳሚክ ባለሙያዎች ሲጠቀም በሥራ ላይ ያሉ ህጎችን በማይቃረን መልኩ ግልጽ መስፈርት በማዘጋጀትና የአሰራር ሥርዓት በመዘርጋት በዩኒቨርሲቲው የሥራ አመራር ቦርድ በማጸደቅ ወደ ተግባር ሊገባ ይገባል፡፡ ህጋዊ ሰውነት ከሌላቸው ማህበራት ጋር የሚያደርጋቸውን ስምምነት ሊያቆም እና ህጋዊ ዕውቅና እና የንግድ ፈቃድ ካላቸው አካላት ጋር ብቻ እንዲሰሩ ውል መግባት ይጠበቅበታል፡፡ በተጨማሪም በጊዜያዊነት ለሚቀጥራቸው ባለሙያዎች የሚከፈል ክፍያ፣ አበል ሆነ ሌላ ወጪዎች መስፈርትና ተመን በማዘጋጀት እና በቦርድ በማጸደቅ ወደ ሥራ ሊገባ እና በሥራ አመራር ቦርዱ ባልጸደቀ መስፈርትና ተመን የሚያደርጋቸውን ክፍያ ሊያቆም ይገባል፡፡
- ኢንተርፕራይዙ የውስጥ ኦዲቱን በማጠናከር በየጊዜው የኢንተርፕራይዙን ሂሳብ እና ንብረት እንዲሁም ሌሎች ተግባራትን ኦዲት በማድረግ ለኢንተርፕራይዙ አመራርም እና ለሥራ አመራር ቦርድ እንዲያቀርብና ክፍተቶች በአፋጣኝ እርምጃ የሚወሰዱበትን ሁኔታ ሊፈጥር ይገባል፡፡
- ኢንተርፕራይዙ የመረጃ አደረጃጀት፣ አያያዝ እና ልውውጥ ስርዓቱን በማዘመን አጠቃላይ የመረጃ አያያዝ ስርዓቱ በዘመናዊ ኢንፎርሚሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ (ICT) የተደገፈ በማድረግ የመረጃ ልውውጥ ስርዓቱ ወጪ ቆጣቢ፣ ፈጣንና ቀልጣፋ እንዲሁም ውጤታማ እንዲሆን ማድረግ እንደሚገባ፤

የሚሉ ናቸው፡፡

ክፍል አንድ

መግቢያ

1. በአምስት ዓመቱ የትምህርት ልማት ሴክተር ዕቅድ (2008-2012) ውስጥ ዩኒቨርሲቲዎች የራሳቸውን ገቢ በማመንጨት ወጪያቸውን በከፊል መሸፈን እንዳለባቸው ከአመራርና አሰራር ብቃት በተጨማሪ የተሻለ የገቢ ማመንጫ ፖሊሲና ሥርዓት ሊኖራቸው እንደሚገባ ትኩረት ተሰጥቷል፡፡ ስለሆነም ወደፊት የሚታሰበው ተጨማሪ የማስፋፋት ተግባራትን ለማሳካት ውጤታማና ቀልጣፋ የበጀት አጠቃቀም ሥርዓት መዘርጋት ብቻ ሳይሆን የበጀት ምንጭንም ማስፋት ያስፈልጋል፡፡ በመሆኑም የፋይናንስ ሥርዓቱን ማሻሻል፣ የፋይናንስ ምንጭን ማበራከት፣ የበጀት አመዳደብና አጠቃቀምን ማሻሻል ቁልፍ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች መሆን አለባቸው፡፡

2. የከፍተኛ ትምህርት ፋይናንስ ተቋማቱ የሚያከናውኑት የመማር ማስተማር፣ የምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት፣ የቴክኖሎጂ ሽግግርና የዩኒቨርሲቲ ኢንዱስትሪ ትስስር፣ የተለያዩ ህንጻዎች ግንባታ፣ ዓለም አቀፋዊ ግንኙነትና አጋርነት፣ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ የመጣን የትምህርት ተሳትፎ እና የትምህርት ጥራት ፍላጎትን ለማሳደግ፣ ወዘተ ሥራ ጋር ተያይዞ የሚጠይቀው በጀት እጅግ ከፍተኛ ከመሆኑ አንጻር መንግሥት የከፍተኛ ትምህርት ዘርፍ ልማትን ለማፋጠን ከራሱ ከሚመደበ በጀት በተጨማሪ የተለያዩ የገንዘብ ምንጮችን በማፈላለግና ከመማር ማስተማሩ በተጓዳኝ ገቢ ማመንጫ በሆኑ ተግባራት ላይ በመሰማራት የታለመውን ግብ ለማሳካት መንቀሳቀስ ይጠበቅባቸዋል፡፡

3. ስለዚህ የዩኒቨርሲቲዎች የውስጥ ገቢን ለማሳደግ መንግስት ከሚመድበ በጀት በተጨማሪ የተለያዩ ኢንተርፕራይዞችን በማቋቋም ከመንግስት ከሚመደበ በጀት ውስጥ የተወሰነውን ለመሸፈን በእቅድ ተይዞ መሰራት አለበት፡፡

4. መንግስትም ለጉዳዩ ትኩረት በመስጠት በከፍተኛ ትምህርት መቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 66፣ በተሻሻለ የከፍተኛ ትምህርት መቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 1152/2011 እንዲሁም የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የገቢ ማስገኛ ድርጅቶች ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 456/2012 መሠረት ዩኒቨርሲቲዎች የራሳቸውን የገቢ ማመንጫ ተቋማትን ማቋቋም እንደሚችሉ ደንግጓል፡፡ በዚህም መሠረት ዩኒቨርሲቲዎች ራሳቸው የሚያመነጩትን የተለያዩ የውስጥ ገቢዎች የሚመሩበት፣

የሚሰበሰቡበት እና ሥራ ላይ የሚያውሉበት የፋይናንስ ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡

5. ስለዚህ የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲም የዩኒቨርሲቲን ገቢ ማስገኛ ፕሮጀክቶችን የበለጠ ለማጠናከር አደረጃጀታቸው ዘመናዊና ህጋዊ አሠራር እንዲኖራቸው ትኩረት በመስጠት የዩኒቨርሲቲው ማኔጅመንትና አስተዳደር ቦርድ የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ የገቢ ማመንጫ ኢንተርፕራይዝ በህጋዊነት በ2007 ዓ.ም እንዲቋቋም አድርጓል፡፡

የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ የገቢ ማመንጫ ኢንተርፕራይዝ አመሰራረት

6. የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ገቢ ማመንጫ ኢንተርፕራይዝ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 66 እንዲሁም በተሻሻለ የከፍተኛ ትምህርት መቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 1152/2011 አንቀጽ 65 መሠረት ዩኒቨርሲቲዎች የየራሳቸውን ገቢ ማመንጫ ኢንተርፕራይዞች ማቋቋም እንደሚችሉ በተደነገገ መሠረት የዩኒቨርሲቲ የገቢ ማመንጫ ክፍሎች በሀብት ማመንጫ (ሪሶርስ ሞባላይዜሽን) ዳይሬክቶሬት ስር ተደራጅተው ተግባራቸውን እየተወጡ ከነበሩት ውስጥ የተወሰኑትን በመያዝ በአንድ ኢንተርፕራይዝ ስር ተሰባስበው በመደራጀት የሀገሪቱ የንግድ ህግ እና ተዛማጅ ህጎች በሚፈቅዱት አግባብ እንዲሰሩ የዩኒቨርሲቲ ማኔጅመንት ኮሚቴ በልዩ ስብሰባ ቃለ-ጉባዔ ቁጥር 02/2007 ሚያዝያ 05 ቀን 2007 ዓ.ም በወሰነው መሰረት በብር 50 ሚሊዮን ካፒታል የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ገቢ ማመንጫ ኢንተርፕራይዝ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር (Hawassa University Revenue Generating Enterprise Private Limited Company (HUREGE) በመባል ተቋቁሟል፡፡

7. የኢንተርፕራይዝ ማህበሩ የተመሰረተ እያንዳንዳቸው ብር 5,000 ሺህ (አምስት ሺህ ብር) ዋጋ ባላቸው አስር ሺህ (10,000) አክሲዮኖች ብር 50,000,000 (ሃምሳ ሚሊዮን ብር) ነው፡፡ የአክስዮን ድርሻን የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ያለው ጠቅላላ የአክሲዮን መጠን 9,990 (ዘጠኝ ሺ ዘጠኝ መቶ ዘጠና) ብር 49,950,000 (አርባ ዘጠኝ ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ሃምሳ ሺ ብር) ያለው ሲሆን እንዲሁም የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ሠራተኞች ሸማቾች ህ/ሥ/ማህበር ያለው ጠቅላላ የአክሲዮን መጠን 10 (አስር) ብር 50,000 (ሃምሳ ሺ ብር) ይዘዋል፡፡ ሁሉም የአክስዮኖች ድርሻ በጥ[illegible] በ2007 ዓ.ም ተከፍሏል፡፡

የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ የገቢ ማመንጫ ኢንተርፕራይዝ ተልዕኮ ራዕይ እና ዓላማ፡-

የኢንተርፕራይዙ ተልዕኮ፡-

8. ገቢ ማመንጨት የሚችሉ ዩኒቶችን በማስፋፋት፣ በአከባቢና በሀገር አቀፍ ደረጃ ካሉ መካከለኛና ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች ጋር ትስስር በመፍጠር፣ አዳዲስ ገቢ ሊያስገኙ የሚችሉ ፕሮጀክቶችን በመንደፍ፣ የምርምርና ማማከር እንዲሁም የገበያ ልማት ጥናት ተግባራትን በማጠናከር፣ ውጤታማና ቀልጣፋ የበጀት አጠቃቀም ሥርዓት መዘርጋትና አስተማማኝ የፋይናንስ ምንጭ ለዩኒቨርሲቲው መፍጠር ነው፡፡

የኢንተርፕራይዙ ራዕይ፡-

9. በ2017 የገቢ ምንጮች ተስፋፍተው፣ ኢንተርፕራይዙ አቅም ፈጥሮ በሀገር አቀፍ ደረጃ የተሻለ ተወዳዳሪ ሆኖ ማየት ነው፡፡

የኢንተርፕራይዙ ዓላማ፡-

10. በዩኒቨርሲቲ ውስጥ የሚገኙ የገቢ ማመንጫ ማዕከላትን በማስፋፋትና እሴት በመጨመር ለዩኒቨርሲቲና ለአካባቢ ማህበረሰብ ብሎም በሀገር አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪና ጥራት ያለው ምርትና አገልግሎት በማቅረብ የኢንተርፕራይዙን ገቢ ማሳደግ ነው፡፡

የኢንተርፕራይዙ የንግድ ስራ ዓላማዎች፡-

- ✓ የብረታ ብረትና የእንጨት ስራ ውጤቶችን በማምረት ስራ መሰማራት፤
- ✓ በአግሪ ቢዝነስ (ለምሳሌ የወተት ከብት እርባታ፣ ወተት ማቀነባበር፣ ከብት ማደለብ፣ የቄራ አገልግሎት፣ የሥጋ ንግድ፣ የአዝርዕት ልማት፣ የጓሮ አትክልት ልማት፣ የዶሮ እርባታ እና የአሳማ እርባታ ወዘተ) ስራዎች ላይ መሰማራት፤
- ✓ የመድሀኒት ቤት እና እንደ አስፈላጊነቱ የህክምና አገልግሎት፤
- ✓ የኮምፒተር ሶፍት ዌር ማበልፀግ (Software Developmenet) እና የተለያዩ የኮምፒተር እና ተዛማጅ ስልጠናዎችን መስጠት፤
- ✓ የሆቴል ንግድ ስራ፤

- ✓ ዳቦ ማምረት፤
- ✓ ከማህበሩ ዓላማ ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ሌሎች የንግድ ስራዎችን መስራት፤
- ✓ የማማከር ስራዎችን በንግድ፣ በልማት፣ በኮንስትራክሽን ስራዎች መሰማራት፤
- ✓ በተለያዩ የግንባታ ስራዎች ተሰማርቶ መስራት፤
- ✓ የነዳጅ ማደያ ማቋቋምና አገልግሎት መስጠት፤
- ✓ የጋራዥ አገልግሎት መስጠት፤
- ✓ የሱፐርማርኬት ንግድ ማካሄድ፤
- ✓ የዩኒቨርሲቲ ማህበረሰብ ትምህርት ቤቶችን ማቋቋም፤
- ✓ የእንግዳ ማረፊያ ቤቶችን (ፔንሲዮን) ማቋቋምና መስራት፤
- ✓ የህትመት ንግድ ስራዎችን ማካሄድ እና
- ✓ ሌሎች ከማህበሩ ዓላማ ጋር ተዛማጅ የሆኑ የንግድ ስራዎችን መስራት፡፡

የመንግስት ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ተግባርና ኃላፊነት

11. የመንግስት ከፍተኛ የትምህርት ተቋማትን እንደገና ለማቋቋም በወጣ አዋጅ ቁጥር 1152/2011 አንቀፅ 8 ንኡስ አንቀፅ 5 መሰረት ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የተለያዩ የገቢ ማመንጫ ስራዎችን የመስራትና ገቢን ለተልዕኮ ማስፈፀሚያ የመጠቀም ነፃነት እና ስልጣን ተሰጥቷቸዋል፡፡

የኢንተርፕራይዙ ቦርድ ተግባርና ኃላፊነት

12. የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የገቢ ማስገኛ ድርጅቶችን ለማቋቋም በወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 456/2012 መሰረት የኢንተርፕራይዙ ቦርዱ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባሮች ተሰጥቷል፡-

- ✓ የገቢ ማስገኛ ድርጅቱን አፈፃፀም በበላይነት ይመራል፤ይቆጣጠራል፤
- ✓ የገቢ ማስገኛ ድርጅቱ በምን ዓይነት የንግድ ስራ ዘርፎች ላይ መሰማራት እንዳለበት፣ በየትኞቹ የአገሪቱ ክፍሎች ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት እንደሚኖር፣ የዩኒቨርሲቲ መምህራንና ተማሪዎች በገቢ ማስገኛ ድርጅቱ ስራ

ስለሚኖራቸው ተሳትፎ እና ስራን ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ ተያያዥ መመሪያዎችን ያፀድቃል፤

- ✓ የገቢ ማስገኛ ድርጅቱን የአገልግሎት አሰጣጥ በሚመለከት የሚቀርቡ ቅሬታዎች የሚስተናገዱበት ሥርዓት መዘርጋቱን ያረጋግጣል፤
- ✓ የገቢ ማስገኛ ድርጅቱን ስራዎች በቅርበት የሚከታተል እና የሚደግፍ ኮሚቴ ያቋቁማል፡፡

የሚሉት ናቸው፡፡

የኢንተርፕራይዙ ዋና ስራ አስኪያጅ ተግባርና ኃላፊነት

13. የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የገቢ ማስገኛ ድርጅቶችን ለማቋቋም በወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 456/2012 መሰረት የኢንተርፕራይዙ ሥራ አስኪያጅ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባሮች ተሰጥቷል፡-

- ✓ ዋና ስራ አስኪያጁ የገቢ ማስገኛ ድርጅቱ ዋና ስራ አስፈፃሚ በመሆን ከዩኒቨርሲቲ በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ መሰረት የገቢ ማስገኛ ድርጅቱን ስራዎች ይመራል፤ ያስተዳድራል፤
- ✓ የገቢ ማስገኛ ድርጅቱን ሰራተኞች በቦርዱ በሚፀድቅ መመሪያ መሰረት ይቀጥራል፤ያስተዳድራል፤
- ✓ የገቢ ማስገኛ ድርጅቱን የስራ ፕሮግራምና በጀት አዘጋጅቶ ለቦርድ ያቀርባል፤ ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤
- ✓ ለገቢ ማስገኛ ድርጅቱ በተፈቀደ በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሰረት ክፍያዎችን ይፈፅማል፤
- ✓ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች የገቢ ማስገኛ ድርጅቱን ይወክላል፤
- ✓ የገቢ ማስገኛ ድርጅቱን የስራ አፈፃፀምና የሂሳብ ሪፖርቶች አዘጋጅቶ ለቦርዱ ያቀርባል፤
- ✓ ለገቢ ማስገኛ ድርጅቱ ስራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ስልጣንና ተግባሩን በከፊል ለገቢ ማስገኛ ድርጅቱ ሌሎች ኃላፊዎችና ሰራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡

የሚሉት ናቸው፡፡

የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ገቢ ማመንጫ ኢንተርፕራይዝ ድርጅታዊ መዋቅር እና የሰው ኃይል አደረጃጀት

የኢንተርፕራይዙ ድርጅታዊ መዋቅር

14. የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ የገቢ ማስገኛ ኢንተርፕራይዝ ተጠሪነቱ ለሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ቦርድ ሆኖ በሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ አቅራቢነት እና በቦርዱ አፅዳቂነት በሚሾም አንድ ዋና ስራ አስኪያጅ፣ አንድ የኦፕሬሽን ዘርፍ ምክትል ስራ አስኪያጅ እና አንድ የአስተዳደርና ፋይናንስ ዘርፍ ምክትል ሥራ አስኪያጅ የሚመራ ሲሆን በዋና ሥራ አስኪያጁ የሚመሩ አምስት፤ በኦፕሬሽን ዘርፍ ምክትል ስራ አስኪያጅ የሚመሩ ሁለት እና በአስተዳደርና ፋይናንስ ዘርፍ ምክትል ሥራ አስኪያጅ የሚመሩ ሶስት የስራ ክፍሎች ተዋቅሯል፡፡ (የኢንተርፕራይዙ ድርጅታዊ መዋቅሩ በአባሪ (1) ተያይዟል፡፡)

የኢንተርፕራይዙ የሰው ኃይል አደረጃጀት

15. የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ የገቢ ማመንጫ ኢንተርፕራይዝ እስከ የካቲት 10 /2015 ዓ.ም ድረስ በጠቅላላ 238 የሰው ሀይል ያለው ሲሆን ከእነዚህ ስጥ 89 ቋሚ ኮንትራት እና 149 የቀን ሰራተኞች ናቸው፡፡ በስራ ላይ ያለው የሰው ሀይል ሴት 93 ወንድ 144 ሰራተኞች በጠቅላላ 238 ነው፡፡

16. የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ የገቢ ማመንጫ ኢንተርፕራይዝ የሰው ሀይል በትምህርት ደረጃ ሲተነተን ደግሞ ማስተርስ 3፣ ዲግሪ 39፣ ዲፕሎማ 12፣ ሰርቲፊኬት 13፣ ሁለተኛ ደረጃ102፣ አንደኛ ደረጃ 66 መሆናቸውን ከኢንተርፕራይዙ ከሰው ሀብት አስተዳደር ከተሰበሰበ መረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡

የኢንተርፕራይዙ የፋይናንስ ምንጭ

17. የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ የገቢ ማመንጫ ኢንተርፕራይዝ በመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የገቢ ማስገኛ ድርጅቶች ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 456/2012 የተሰጠውን ስልጣንና ተግባር ወጪን የሚሸፍን ኢንተርፕራይዙ ከሚያገኘ ገቢ ነው፡፡

የጀት ዓመት	የገቢ ዕቅድ	የወጪ ዕቅድ	የተገኘ ገቢ	የወጣ ወጪ
2012 ዓ.ም	87,340,620	71,479,518.76	-	-
2013 ዓ.ም	75,275,640.00	61,913,328.36	55,524,529.71	-
2014 ዓ.ም	85,182,600.00	63,950,918.25	87,805,420.07	66,339,206.19

የኢንተርፕራይዙን የ2012 ዓ.ም የተገኘ ገቢ እና የወጣ ወጪን መረጃ ለማግኘት ባለመቻሉ ማወቅ አልተቻለም፡፡ በተጨማሪም የ2013 ዓ.ም የወጣ ወጪ መረጃ መግኘት አልተቻለም፡፡

የኢንተርፕራይዙ የአሰራር ስርዓት መግለጫ

የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ የገቢ ማመንጫ ኢንተርፕራይዝ በ2007 ዓ.ም ተቋቁሞ በተለያዩ የንግድ ዘርፎች ላይ አገልግሎት ለመስጠት አራት የገቢ ማመንጫ ማዕከላት ያሉት ሲሆን እነርሱም፡-

1. **በእርሻ ማዕከል፡-** በዕርሻ ማዕከል ስር የከብት እርባታ፣ የዶሮ እርባታ፣ ፍየል እርባታ እና የወተት ማቀነባበር ስራዎች እንዲሁም የጓሮ አትክልቶችን እና ጥራጥሬዎች ይመረታሉ፤
2. **የወንዶ ገነት ደንና ተፈጥሮ ሀብት ኮሌጅ ዕደ-ጥበብ ማዕከል፡-** የብረታብረት እና የእንጨት ውጤቶችን የማምረት ስራ፤
3. **የግብርና ኮሌጅ ዕደ ጥበብ ማዕከል፡-** የብረታብረት እና የእንጨት ውጤቶችን የማምረት ስራ፤
4. **የሆቴል አገልግሎት ማዕከል፡-** የመኝታ፣ ምግብ እና ሻይ ቡና አገልግሎት መስጠት፤

   በተጨማሪም ኢንተርፕራይዙ የዩኒቨርሲቲ መምህራኖችን በመጠቀም የማማከር አገልግሎት ስራዎችን በሃና ሃነክ ምህንድስና እና በአርክቴክት፤ ዲዛይን ስትርኪቸርን ስራዎች ላይ የማማከር ስራዎችን እየሰራ ይገኛል፡፡

የኦዲቱ ዓላማ

18. የክዋኔ ኦዲቱ ዓላማ የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ የገቢ ማመንጫ ኢንተርፕራይዝ የገቢ ማመንጫ ሥራዎችን ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ በሆነ መንገድ በማከናወን እና ትርፋማ በመሆን ዩኒቨርሲቲ የተቋቋመበትን ተልእኮ እና አላማ ለማሳካት እንዲረዳ የሚያፈልግ የፋይናንስ ምንጭ ለመሆን እየሠራ መሆኑን ለማረጋገጥ ሲሆን ይህ ሆኖ ካልተገኘ የአሰራር ግድፈቶችን ለይቶ በማውጣት ግድፈቶቹን ለማስወገድ ወይም ለመቀነስ የሚያስችል የማሻሻያ ሀሳቦችን በማቅረብ እና ተጠያቂነትን ለማጠናከር ነው፡፡

የኦዲት አካባቢ (Audit Area)

19. የኦዲት ቡድኑ ከላይ የተጠቀሱትን ዘዴዎች በመጠቀም "የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ የገቢ ማመንጫ ኢንተርፕራይዝ እና የውስጥ ገቢ አፈፃፀም ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ መሆኑን በተመለከተ መገምገም" የሚል ነው፡፡

የኦዲት ትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issues)

20. ከላይ የተገለጸን የኦዲት አካባቢ ኦዲት ለማድረግ ሶስት ትኩረት አቅጣጫ (Audit Issues) የተመረጡ ሲሆን፤ እነርሱም፡-

   I. የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ የገቢ ማመንጫ አስተዳደር እና አሰራር የሀገሪቱን ህግና ስርዓትን የተከተለ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ መሆኑን መገምገም፤

   II. የገቢ ማመንጫ ኢንተርፕራይዙ የገቢ ማመንጫ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የተዘረጋ ሥርዓት ኢኮኖሚያዊ ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መልኩ መከናወኑን መገምገም፣

   III. የገቢ ማመንጫ ኢንተርፕራይዙ የሀብት አስተዳደር፣ የገቢያ ጥናት እና መረጃ አያያዝና ልውውጥ ስርዓት በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ መሆኑን መገምገም፣

የኦዲት መመዘኛ መስፈርት (Audit Evaluative Criteria

21. ከላይ የተጠቀሱትን የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issue) ለመመዘን የሚረዱ 30 የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (evaluative critera) የተዘጋጁ ሲሆን፣ በተዘጋጁት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎችና የመመዘኛ መስፈርቶች ላይም የኢንተርፕራዙ የበላይ ኃላፊዎች አስተያየት እንዲሰጡበት የተደረገ ሲሆን የኢንተርፕራዙ የበላይ ኃላፊዎች መስፈርቶቹ ላይ እንደተስማሙ በደብዳቤ ገልጸዋል፡፡ መመዘኛ መስፈርቶቹ ከዚህ ሪፖርት ጋር በአባሪ (2)ተያይዟል፡፡

22. የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶቹን ለማዘጋጀት በዋናነት መሰረት የሆኑት የከፍተኛ ትምህርት አዋጅ 1152/2011፣ የመንግስት ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የገቢ ማስገኛ ድርጅት ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 456/2012፣ የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የገቢ ማስገኛ ድርጅቶች የሚተዳደሩበትን ሥርዓት ለመወሰን የወጣ ቁጥር 04/2014፣ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የውስጥ ገቢ መመ ቁጥር 39/2006፣ የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ የገቢ ማመንጫ ኢንተርፕራዝ እቅድ እና

አፈፃፀም ሪፖርቶች እና ሌሎች ተያያዥ የሆኑ አዋጆችና መመሪያዎች እንዲሁም መልካም ተሞክሮዎች ናቸው፡፡

የኦዲት ወሰንና ዘዴ

የኦዲቱ ወሰን

23. ኦዲቱ የተከናወነ በአለም አቀፍ የዋና ኦዲተር መ/ቤቶች (INTOSAI) የክዋኔ ኦዲት ደረጃዎች (ISSAI) እና ለመ/ቤታችን በአዋጅ ቁጥር 982/2008 በተሰጠ ሥልጣን መሰረት ነው፡፡ ኦዲቱ የሚሸፍነ ከ2012 ዓ.ም እስከ 2014 ድረስ ያሉ በጀት ዓመታትን እና የ2015 ዓ.ም የግማሽ ዓመት የስራ አፈፃፀምን በማካተት ተከናውኗል፡፡ የኦዲት ስራ የሚያተኩረው የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ የገቢ ማመንጫ ኢንተርፕራይዝ እና የውስጥ ገቢ አፈጻጸምን በተመለከተ ሲሆን በዋናነት ኦዲቱ የሚከናወነው በሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ዋና መ/ቤት ሲሆን ከዋና መ/ቤት በተጨማሪ በኢንተርፕራይዙ ማዕከላት እና በዩኒቨርሲቲ በናሙና በተመረጡ ኮሌጆች መረጃ ተሰብስቧል፡፡

የኦዲቱ ዘዴ

24. ኦዲቱ የተከናወነው ከኦዲት ስራ ጋር ተያያዥነት ያላቸው መረጃዎች፣ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት አዋጅ፣ የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የገቢ ማስገኛ ድርጅቶች ደንብ፣ የኢንተርፕራይዙ የመመስረቻ ፅሁፍና የመተዳደሪያ ደንብ፣ በኢንተርፕራይዙ የወጡ የተለያዩ የአሰራር ማንዋሎች እና መመሪያዎች፣ የኢንተርፕራይዙ የቦርድ ቃለ-ጉባኤዎች፣ የኢንተርፕራይዙ የማኔጅመንት ቃለ-ጉባኤዎች እና ከ2012 ዓ.ም- 2015 ዓ.ም ድረስ የተዘጋጁ ዕቅድና የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርቶች በመከለስ ፣ በኢንተርፕራይዙ ስር ያሉ የአራት ማዕከላት ኃላፊዎችን ቃለ- መጠይቅ በማድረግ እንዲሁም የውስጥ ገቢ ማመንጫን በተመለከተ ለሪሶርስ ሞባላይዜሽን ዳይሬክቶሬት እና ለበላይ ኃላፊዎች እና በኮሌጆች ስር በሚገኙ የውስጥ ገቢ የስራ ሂደቶች ቃለ-መጠይቅ በማቅረብና መረጃ በመሰብሰብ ተከናውኗል፡፡ የተከለሱ መረጃዎች ዝርዝር በአባሪ (4) ተያይዟል፡፡

ክፍል ሁለት

ግኝቶች

2.1 የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ የገቢ ማመንጫ አስተዳደር እና አሰራር የሀገሪቱን ህግና ስርዓትን የተከተለ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ መሆኑን መገምገም፤

የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ የገቢ ማመንጫ ኢንተርፕራይዝ ተጠሪነትን በተመለከተ፡-

25. የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ የገቢ ማመንጫ ኢንተርፕራይዝ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 456/2012 ዓ.ም መሰረት ዩኒቨርስቲን በበላይነት ለሚያስተዳድር ቦርድ ተጠሪ ሆኖ ሊቋቋም ይገባል፡፡

26. የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ የገቢ ማመንጫ ኢንተርፕራይዙ በ2007 ዓ.ም ሲቋቋም ተጠሪነቱ ለዩኒቨርስቲ ፕሬዚዳንት ሆኖ የተቋቋመ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ አዲስ በወጣ የ2012 ዓ.ም የገቢ ማስገኛ ድርጅቶች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 456/2012 አንቀፅ 5 ንኡስ አንቀፅ 1 እና አንቀፅ 6 ንኡስ አንቀፅ 1 መሰረት እንዲሁም የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የገቢ ማስገኛ ድርጅቶች የሚተዳደሩበትን ሥርዓት ለመወሰን በወጣ መመሪያ ቁጥር 04/2012 አንቀጽ 7(1) የሁሉም የመንግስት ዩኒቨርሲቲ የገቢ ማስገኛ ኢንተርፕራይዞች ተጠሪነታቸው ዩኒቨርሲቲውን ለሚያስተዳድረው የሥራ አመራር ቦርድ እንዲሆን በተደነገገው መሰረት ዩኒቨርሲቲን ለሚያስተዳድረው ቦርድ ተጠሪ ሆኖ ያልተቋቋመ መሆኑን በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

27. ስለጉዳዩ የኢንተርፕራይዙ የበላይ ኃላፊ በቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ፣ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት መልስ የኢንተርፕራይዙ በአዲስ መልክ ለቦርድ ተጠሪ ሆኖ ያልተቋቋመ የኢንተርፕራይዙ መዋቅር ባለመጠናቱ እና መዋቅሩን ለማጥናት ረጅም ጊዜ እንደፈጀ እና አሁን ላይ የተጠና ቢሆንም በቦርድ አለመጽደቁን በዚህም እስካሁን ለቦርድ ተጠሪ ሆኖ አለመቋቋሙን ገልጸዋል፡፡

28. በተጨማሪም የሀዋሳ ዩኒቨርስቲ ፕሬዝዳንት እና የኢንተርፕራይዙ የበላይ ኃላፊ በመውጫ ስብሰባ እና በተላከላቸው የረቂቅ ሪፖርት ላይ በጽሁፍ በሰጡት መልስ በደንቡና በመመሪያው መሰረት ኢንተርፕራዙ ለቦርድ ተጠሪ ሆኖ ለመቋቋም የመዘግየት ሁኔታ መኖሩን ገልጸዋል፡፡ የገቢ ማመንጫ ድርጅቶች ተጠሪነታቸውን በተመለከተ በገንዘብ ሚኒስቴር፤ በትምህርት ሚኒስቴር እና በዋና ኦዲተር በኩል አለመግባባት እንደነበር እና በህጉ መሰረት በሪፖርቱ ላይ የተጻፈ ነገር ልክ እንደሆነ

ነገር ግን ህጉ ላይ መጀመሪያ በረቂቁ ላይ ስንወያይ የተስማማንበት እና መሆን የነበረበት ኢንተርፕራይዙ ተጠሪነቱ ለቦርድ ሳይሆን ለዩኒቨርስቲው መሆን እንደነበረበት ነገር ግን ሲጸድቅ ተጠሪነቱ ለቦርድ እንዲሆን በመደረጉ በዚህም የህግ አቀራረጹ ልክ እንዳልሆነ ገልጸዋል፡፡ የኢንተርፕራይዙን መዋቅር በ2012 ዓ.ም ለማስጠናት ሁለት ጊዜ የጨረታ ሰነድ አውጥተው ኢስት አፍሪካ ኮንሰልቲንግ ኃላ/የተ/የግ/ማህበር እንዲያጠና ተሰጥቶ ነገር ግን በኮቪድ ወረርሽኝ ምክንያት ጥናቱ ሳይጠናቀቅ ረጅም ጊዜ የፈጀ መሆኑን በዚህም ጥናቱ በ2014 ዓ.ም ተጠናቆ ለቦርድ እንደቀረበ እና ተጠሪነቱን ውክልና ለዩኒቨርስቲው እንዲሰጥ ጥያቄ ያቀረቡ መሆኑን ነገር ግን እስካሁን ውክልና እንዳልተሰጠ ገልጸዋል፡፡ ኃላፊዎቹ ይህንን ምላሽ ቢሰጡም በወጣ ህግ መሰረት ለዩኒቨርሲቲው ቦርድ ተጠሪ ሆኖ መቋቋም እንዳለበት በመደንገጉ እና ህጉ ከወጣ ሦስት አመት ያለፈ በመሆኑ፣ እና ኢንተርፕራይዙ ለዩኒቨርስቲው ተጠሪ እንዲሆን ለቦርድ ጥያቄ የቀረበበት ሰነድ እንዲሁም የኢንተርፕራይዙ መዋቅር ጥናት በወቅቱ ማለቅ ስለነበረበት እና አሁንም ቢሆን የድርጅቱ የመዋቅር ጥናት ስለመጠናቀቁ የሚያሳይ ማስረጃ ባለመቅረቡ የተሰጠ ምላሽ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

29. ኢንተርፕራይዙ በከፍተኛ ትምህርት የገቢ ማስገኛ ድርጅቶች ማቋቋሚያ ደንብ መሰረት ለቦርድ ተጠሪ ሆኖ አለመቋቋሙ በደንቡና በመመሪያ ላይ የተሰጠውን ኃላፊነት እንዳይወጣና ስራዎችን በአግባቡ እንዳይሰራና ተጠያቂነት እንዳይጠናከር አድርጓታል፡፡

የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ የገቢ ማመንጫ ኢንተርፕራይዝ ካፒታል በተመለከተ፤

30. የገቢ ማመንጫ ኢንተርፕራይዙ ሲቋቋም ከዩኒቨርሲቲ በአይነት የተሰጡ ንብረቶችና ሀብቶች በባለሙያዎች በትክክል ተገምተና በኦዲተር ተረጋግጦ የኢንተርፕራይዙ ካፒታል አካል ሆኖ ሊቋቋም ይገባል፡፡ በተጨማሪም በደንብ ቁጥር 456/2012 ዓ.ም አንቀጽ 12 1 እና 2 እንዲሁም የገቢ ማስገኛ መተዳደሪያ መመሪያ ቁጥር 02/2012 ዓ.ም አንቀጽ 7(1) መሰረት የኢንተርፕራይዙ ካፒታል በገለልተኛ ባለሙያ ሊገመትና በኦዲተር ተረጋግጦ ካፒታሉ እንደገና ሊከለስ ይገባል፡፡

31. ይሁን እንጂ፡-

- የገቢ ማመንጫ ኢንተርፕራይዙ በ2007 ዓ.ም ሲቋቋም በጥሬ ገንዘብ [illegible] ካፒታል በተጨማሪ ከዩኒቨርሲቲ በአይነት የተሰጡት የገቢ ማስገኛ ማዕከላት ማለትም (የእርሻ ማዕከል፣ የሆቴል አገልግሎት ማዕከል፣ የግብርና ኮሌጅ

የእንጨት እና ብረታ ብረት ዕደ-ጥበብ ማዕከል እንዲሁም የወንዶገነት የእንጨት እና ብረታ ብረት ዕደ-ጥበብ ማዕከል) ንብረቶች በባለሙያ በትክክል ተገምቶና በኦዲተር ተረጋግጦ በወቅቱ በነበረ የገበያ የዋጋ ተመን መሰረት ምን ያህል ዋጋ እንዳላቸው በትክክል ታውቀ ወደ ኢንተርፕራይዙ ካፒታል ውስጥ ያልተካተቱ መሆኑን፤

- የኢንተርፕራይዙ የ2009 በጀት አመት የውጭ ኦዲት ሪፖርት ላይ የተዘዋወሩት ቋሚ ንብረቶች ዋጋ አጠቃላይ ግምታቸው ብር 76,316,018.00 እንደሆነ የተገለጸና የዋጋ ግመታው ለሥራ ፈቃድ በተሰጠው እና የራሱ የሆነ ኃላፊነት ባለው ተቋም እንዲከናወን መግባባት ላይ መደረሱን የኢንተርፕራይዙ የሥራ አመራር ቦርድ ጥር 25 ቀን 2010 ዓ.ም. ወስኖ ነበር፡፡ በሥራ አመራር ቦርዱ ውሳኔ መሰረት ንብረቶቹ ፈቃድ በተሰጠው አካል ተገምተው በኢንተርፕራይዙ ካፒታል ውስጥ እንዲካተቱ ያልተደረገ መሆኑን፤

በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

32. ስለ ጉዳዩ ለኢንተርፕራይዙ የበላይ ኃላፊዎች በቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ እና በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት መልስ ኢንተርፕራይዙ በ2007 ዓ.ም ሲቋቋም በግብርና ኮሌጅ እና በወንዶ ገነት ዕደ-ጥበብ ማዕከል ያሉ ማሽነሪዎች የቆይታ ጊዜያቸው ረጅም ጊዜ የቆዩ አሁን ላይ ዋጋቸው በትክክል የማይታወቅ መሆኑ፣ በውጭ እርዳታ የመጡ እንዲሁም የቅናሽ ዋጋቸውን ለመገመት አዳጋች በመሆኑ በዩኒቨርሲቲ አመራር ከየዘርፉና ከየሙያ የተወጣጣ አንድ ኮሚቴ ተሰይሞ ግምት ሰርተው፣ ተመን አውጥተው፣ ዶክመንት ተዘጋጅቶ የተላለፈ መሆኑን እንዲሁም የኢንተርፕራይዙ መዋቅር ተጠንቶ ባለመጽደቁ በአዲስ ደንብና መመሪያ ካፒታሉ ተረጋግጦ ያልተቋቋመ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ በተጨማሪም የኢንተርፕራይዙ የበላይ ኃላፊ እና የሀዋሳ ዩኒቨርስቲ ፕሬዝዳንት በመውጫ ስብሰባ እና በተላከላቸው ረቂቅ ሪፖርት ላይ በጽሁፍ በሰጡት መልስ የኢንተርፕራይዙ የካፒታል መነሻን በተመለከተ በገለልተኛ አካል ይተመን የሚለው ላይ ገለልተኛ አካል የሆኑ እና ሰርቲፋይድ የሆነ ገማች ተቋም መጥፋቱን እንደማያውቁ፣ ነገር ግን በአይነት ለኢንተርፕራይዙ የተላለፉ ንብረቶች ወደ ኢንተርፕራይዙ ካፒታል አለመካተታቸው ግኝቱ ትክክል መሆኑን እና እንደተቀበሉት እንዲሁም ወደ ፊት እንደሚያስተካክሉ ገልጸዋል፡፡

33. የኢንተርፕራይዙ የበላይ ኃላፊ ይህን ይበሉ እንጂ በ2009 ዓ.ም የዩኒቨርስቲ አመራር ኮሚቴ የንብረት ቆጠራ እና የቋሚ ንብረቶች የዋጋ ግምት ሲሰራ የዋጋ ግመታ

ትክክል ስለመሆኑ እንዲሁም ድርጅቱ በአይነት የተረከባቸውን የንብረት አይነቶች ፊቃድ በተሰጠ ባለሙያ በወቅቱ በነበረ ተመሳሳይ ዋጋ ተገምተው እና በኦዲተር ተረጋግጦ በጥሬ ገንዘብ ከተከፈለ የመቋቋሚያ ካፒታሉ ጋር መካተት ስለነበረባቸው እና እስከ አሁን ድረስ እየተገለገለባቸው ያለ በመሆኑ የተሰጠውን መልስ አልተቀበልነውም፡፡

34. የሀዋሳ ዩኒቨርስቲ የገቢ ማመንጫ ኢንተርፕራይዝ ካፒታል በባለሙያ እና በኦዲተር ተረጋግጦ ባለመቋቋሙ አጠቃላይ ካፒታሉ በትክክል እንዳይታወቅ ከማድረጉም ሌላ የኢንተርፕራይዙን ካፒታል ዝቅ እንዲል አድርጓታል፡፡

የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ የገቢ ማመንጫ ኢንተርፕራይዝ ከሚያገኘው ትርፍ ላይ ለዩኒቨርሲቲው ተልዕኮና አላማ ማስፈጸሚያ ያዋለ መሆኑን በተመለከተ፡-

35. የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የገቢ ማስገኛ ድርጅቶች የሚተዳደሩበት መመሪያ ቁጥር 04/2012 አንቀጽ 7 እና አንቀጽ 8 (1) እና (2) መሰረት የኢንተርፕራይዙ መቋቋሚያ ካፒታል በቦርድ ሲወሰን እና ከተወሰነበት ጊዜ አንስቶ በአምስት አመት ውስጥ ተከፍሎ መጠናቀቅ እንዳለበት እንዲሁም ድርጅቱ በየዓመቱ ከሚያገኘው የተጣራ ትርፍ የተወሰነ የካፒታል ጣራ እስኪደርስ ከትርፉ 60 ከመቶ እና የካፒታል ጣራ ከተሟላ በኋላ ደግሞ የትርፉን 80 ከመቶ ለዩኒቨርሲቲ ተልዕኮ እና ዓላማ ማስፈጸሚያ ሊያውል ይገባል፡፡

36. የኢንተርፕርራይዙ ማቋቋሚያ ካፒታል በ2007 ዓ.ም በጥሬ ገንዘብ 50,000000 (ሀምሳ ሚሊዮን) ብር ተከፍሎ የተጠናቀቀ ሲሆን ካፒታሉ እንደገና እንዲሻሻል ያልተደረገ መሆኑ ታቋውል፡፡

- ይሁን እንጂ ኢንተርፕራይዙ ለገቢዎች ሚኒስቴር በራሱ ባዘጋጀው የሂሳብ መግለጫ ላይ ባሳወቀው መሰረት፡-
    - በ2012 በጀት ዓመት የተጣራ ትርፍ ብር 1,913,716.48
    - በ2013 በጀት አመት የተጣራ ትርፍ ብር 710,045.74
    - በ2014 በጀት ዓመት በኪሳራ ብር (5,269,567.96) ያሳወቀ ሲሆን፤

በ2012 ዓ.ም እና በ2013 ዓ.ም ካገኘው ትርፍ ላይ 80 ከመቶ ኢንተርፒይዙ ለዩኒቨርሲቲ ተልዕኮና አላማ ማስፈጸሚያ ያላዋለ መሆኑን በኦዲት ወቅት ከተከለሱ ሰነዶች ለማወቅ ተችሏል፡፡

37. ስለጉዳዩ የኢንተርፕራይዙ የበላይ ኃላፊ በቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ የገቢ ማመንጫ ኢንተርፕራይዙ አዲስ በወጣው ደንብና መመሪያ መሰረት ባለመቋቋሙ መሆኑን እና በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት መልስ የኢንተርፕራይዙ የግዥና የፋይናንስ የአሰራር መመሪያዎች ባለመጽደቃቸው የትርፍ አጠቃቀም እና ዩኒቨርሲቲው የተበደረውን ገንዘብ የሚመለስበት እንዲሁም የኢንተርፕራይዙ ካፒታል የሚያድግበት አሰራር በኢንተርፕራይዙ የፋይናንስ መመሪያ መሰረት ምላሽ ለመስጠት የመመሪያ መጽደቅ እየተጠበቀ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

38. በተጨማሪም በመውጫ ስብሰባ ወቅት እና በተላከላቸው ረቂቅ ሪፖርት ላይ በሰጡት መልስ ዩኒቨርስቲው በአዲስ አበባ ከተማ በ3800 ካሬሜትር ቦታ ላይ ያረፈን ቤት ሲገዛ ለወደፊት ኢንተርፕራይዙ ከሚያገኘው ትርፍ ለዩኒቨርስቲ ከሚከፍለው ሂሳብ ታሳቢ እንዲደረግ በዩኒቨርስቲ አመራር ተወስኖ የተገዛ መሆኑን እና ህጋዊ አካሄዱን በሚመለከት ኢንተርፕራይዙ ትርፍ የሚያገኝ ከሆነ ለዩኒቨርስቲ ስራ አመራር ቦርድ ቀርቦ እንዲወሰን እንዲሚያደርጉ ገልጸዋል፡፡ የበላይ ኃላፊዎቹ ይህን ምላሽ ቢሰጡም ኢንተርፕራይዙ ከሚያገኘ ትርፍ ላይ ታሳቢ እንዲደረግ በዩኒቨርስቲው ስራ አመራር ስለመወሰኑ የሚያሳይ ማስረጃ ባለመቅረቡ እንዲሁም የአዲስ አበባ ቤት ግዥ ከኢንተርፕራይዙ ካፒታል ላይ የተከፈለ እንጂ ከዩኒቨርስቲው አካውንት ላይ ያልተከፈለ በመሆኑ እና ቤቱ በዩኒቨርስቲ ስም የተመዘገበ ስለሆነ የተሰጠውን ምላሽ አልተቀበልነውም፡፡

39. የኢንተርፕራይዙ በህጉ መሰረት ትርፉ በገለልተኛ ኦዲተር ተረጋግጦ እና በዩኒቨርሲቲ ቦርድ ተወስኖ ከሚያገኘው ትርፍ ላይ ለዩኒቨርሲቲው አላማ እና ተልዕኮ ማስፈጸሚያ እንዲያውል መደረጉ ለዩኒቨርሲቲው ተልዕኮ መሳካት አስተዋጽኦ እንዲያደርግ አድርጓታል፡፡

ኢንተርፕራይዙ በየአመቱ ሂሳቡን እየዘጋ ኦዲት ማስደረጉን በተመለከተ፣

40. በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 1152/2011 ዓ.ም አንቀጽ 64 ንዑስ አንቀጽ 8 እና በመንግስት የከፍተኛ ትምህርት የገቢ ማስገኛ ድርጅቶች የሚተዳደሩበት መመሪያ ቁጥር 04/2012 ዓ.ም አንቀጽ 9(1) እና (2) መሰረት ኢንተርፕራይዙ በIFRS የሂሳብ አመዘጋገብ ስርዓት መሰረት የሂሳብ መዛግብት ሊይዝና በየበጀት አመቱ የሒሳብ መግለጫዎቹን ኦዲት ሊያስደርግ ይገባል፡፡

41. ይሁን እንጂ ኢንተርፕራይዙ ከ2012 ዓ.ም ጀምሮ አመታዊ ሂሳቡን በሚያዘው በአይኤፍ አርኤስ (IFRS) የፋይናንስ አመዘጋገብ ስርዓት መሰረት ሂሳቡን

የሚይዘው መሆኑን እንዲሁም በየአመቱ የሂሳብ መግለጫውን ትክክለኛነት በዋና ኦዲተር ወይም ዋና ኦዲተር በሚሰይመው አካል ኦዲት እየተደረገ የሚይረጋገጥ መሆኑን በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

42. ስለጉዳዩ የኢንተርፕራይዙ የበላይ ኃላፊዎች በቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ የድርጅቱ ሂሳብ በGAAP የፋይናንስ አሰራር የሚከናወን መሆኑን ነገር ግን በIFRS የአመዘጋገብ ስርዓት ያልተመዘገበ በወጣ መመሪያ መሰረት ተግባራዊ አለመደረጉን እና ስለ ሂሳብ አመዘጋገብ ስርዓቱ ስልጠና ባለመሰጠቱ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

43. በተጨማሪም የኢንተርፕራይዙ የበላይ ኃላፊ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት መልስ በIFRS መሰረት የሂሳብ መዛግብትን ለመያዝ በቀጣይነት የመዋቅሩን መጽደቅ እየጠበቁ መሆኑንና በመዋቅሩ ለሚመደቡ ባለሙያዎች ስልጠና ተሰጥቶ ወደ ስራ የሚገባበት መሆኑን እንዲሁም ኦዲትን በሚመለከት በየዓመቱ የሂሳብ መግለጫን ትክክለኛነት ከአዲሱ ደንብ በፊት በውጪ ኦዲተሮች ኦዲት ሲደረግ ቆይቷል በማለት ገልጸዋል፡፡

44. የኢንተርፕራይዙ የበላይ ኃላፊዎች በተላከላቸው የረቂቅ ሪፖርት ላይ በሰጡት ምላሽ ኢንተርፕራይዙ ከተቋቋመበት ጊዜ አንስቶ እስከ 2013 ዓ.ም ድረስ በውጭ ኦዲተር ጨረታ በማውጣት ሂሳቡን ያስመረመረ መሆኑን እና በደንብ 456/2012 ዓ.ም መሰረት በዋና ኦዲተር በተሰየመ ኦዲተር ከ2014 ዓ.ም ጀምሮ ሂሳቡ እንደሚመረመር እና ተግባራዊ እንደሚደረግ ገልጸዋል፡፡

45. የኢንተርፕራይዙ የፋይናንሻል ሂሳብ መግለጫ በውጭ ኦዲተር ከ2011 እስከ 2013 ዓ.ም ድረስ ያለው ኦዲት የተደረገ ስለመሆኑ ማስረጃ ቢቀርብም ነገር ግን በገቢ ማመንጫ ድርጅቶች ማቋቋሚያ ደንብና መመሪያ መሰረት ዋና ኦዲተር ወይም በዋና ኦዲተር በተሰየመ የውጭ ኦዲተር ሂሳቡ ኦዲት እንዲደረግ ለምን እንዳላደረጉ ምላሽ አልሰጡም፡፡

46. ኢንተርፕራይዙ ድርጅቶች በሚጠቀሙበት የአይ.ኤፍ.አር.ኤስ (IFRS) የሂሳብ አመዘጋገብ ስርዓት መሰረት ሂሳቡን ባለመዝጋቱ እና ኦዲት ባለማስደረጉ የኢንተርፕራይዙ የሂሳብ መግለጫ ትክክለኛነት እንዳይረጋገጥ እና አስተማማኝ እንዳይሆን አድርጓታል፡፡

ኢንተርፕራይዙ በሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ያሉ ባለሙያዎችን ለመጠቀም ግልጽ የሆነ መስፈርት አውጥቶ ተግባራዊ ማድረጉን በተመለከተ፡-

47. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 456/2012 አንቀጽ 6 (2)እና የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የገቢ ማስገኛ ድርጅቶች የሚተዳደሩበትን ሥርዓት ለመወሰን በወጣ መመሪያ ቁጥር 4/2012 ዓ.ም አንቀጽ 6(2) መሰረት ኢንተርፕራይዙ በሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ያሉ መምህራንን እና ተመራማሪዎችን እንዲሁም ሌሎች ባለሙያዎችን በጊዜያዊነት እንዴት እንደሚጠቀምባቸው መመሪያ/ መስፈርት አዘጋጅቶና በዩኒቨርሲቲ የሥራ አመራር ቦርድ አጸድቆ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ በተጨማሪም የዩኒቨርሲቲ ባለሞያዎችን ሲጠቀም የኮንትራት አሰጣጥ እና ክፍያ አተማመን ህጋዊ የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

48. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 456/2012 አንቀጽ 6 (2) የዩኒቨርሲቲ ቦርድ የዩኒቨርሲቲ መምህራንና ተመራማሪዎች በገቢ ማገኛ ድርጅቱ ስለሚኖራቸው ተሳትፎና ስራን ለማስፈጸም የሚያፈልጉ ተያያዥ መመሪያዎችን እንደሚያጸድቅ ሲደነግግ እንዲሁም የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የገቢ ማስገኛ ድርጅቶች የሚተዳሩበትን ሥርዓት ለመወሰን በወጣ መመሪያ ቁጥር 4/2012 በዩኒቨርሲቲ ተቀጣሪዎች በገቢ ማገኛ ድርጅቱ ተቀጣሪ ሆነ ማገልገል እንደማይችሉ ይደነግጋል፡፡ ይሁን እንጂ፡-

- ኢንተርፕራይዙ የዩኒቨርስቲን መምህራኖችና ተመራማሪዎች እንዴት እንደሚጠቀምባቸው መመሪያ/መስፈርት ሳያወጣና በቦርድ ሳያጸድቅ ማለትም (የሀዋሳ ዩኒቨርስቲ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት የገና ሃ ነክ መሃንዲሶች አጠቃላይ የሃ ሀብት ልማት አማካሪ ማህበር እና የቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት አጠቃላይ የሲቪልና ተዛማጅ ስራዎች ዲዛይን፣ ሱፐርቪዥንና አማካሪ ማህበር) ጋር ውል በመፈራረም በማማከር አገልግሎት ላይ የሚጠቀም መሆኑን ነገር ግን ማህበራቱ ህጋዊ ሰውነት ያላቸው እና በህግ ሥልጣን በተሰጠው አካል በማህበርነት ስለመደራጀታቸው ማስረጃ ተጠይቆ ያልቀረበ እና የንግድ ፈቃድ የሌላቸው መሆኑን ይልቁንም የኢንተርፕራይዙን ንግድ ፈቃድ የሚጠቀሙ መሆኑ፤
- ኢንተርፕራይዙ በየዩኒቨርሲቲው መምህራኖችና ተመራማሪዎች በማማከር አገልግሎት ላይ ሲጠቀም በገባ ውል መሰረት ስራ ተጠናቆ ከሚገኘው ትርፍ የዩኒቨርስቲው መምህራን 85% የትርፍ ድርሻ ሲኖራቸው ኢንተርፕራይዙ ደግሞ 15% ብቻ የትርፍ ድርሻ ያለ እንዲሆን የተስማማ መሆኑ፤

- ኢንተርፕራይዙ በማማከር አገልግሎት የዩኒቨርስቲውን መምህራን ተጠቅሞ ኢንተርፕራይዙ ከተቋቋመ ጊዜ ጀምሮ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ከብር 59,828,688.42 በላይ ኢንተርፕራይዙ ውል በመግባት ማህበራት ናቸው ለተባሉት እንዲሰሩ የሰጠው እና ክፍያ የፈጸመላቸው መሆኑ፤
- ኢንተርፕራይዙ የመንግስት ሰራተኞች የቀን ውሎ አበል መመሪያን የሚጠቀም መሆኑን ባዘጋጀ የሰው ሀብት አስተዳደር መመሪያ ላይ ያስቀመጠ ሲሆን በተግባር ግን በመስክ አገልግሎት ላይ ለሚሠማሩ ባለሙያዎችና የአስተዳደር ሠራተኞ እንዲሁም ሌሎች ተሳታፊዎች በቀን ብር 850 የውሎ አበል የሚከፈል ሲሆን የአበል ተመኑ በዩኒቨርሲቲው የሥራ አመራር ቦርድ ያልጸደቀ መሆኑ፤
- ኢንተርፕራይዙ የአሞ-ጊቤ ተፋሰስ ላይ የውሃ አቅም እና ነባር የመጠጥ ውሃ ተቋማት ያሉበትን ደረጃ ለማጥናት ለተሳተፉ ባለሙያዎች ብር 968,523.85 እና የአስተዳደር ሰራተኞች ብር 46,550 በድምሩ ብር 1,015,073.85 የቦነስ ክፍያ በማለት በታህሳስ 14 ቀን 2015 የተከፈለ ሲሆን የቦነስ ክፍያ በዩኒቨርሲቲ የስራ አመራር ቦርድ ያልተፈቀደ መሆኑ፤

ታቋል፡፡ (ዝርዝሩ በአባሪ 3 ተያይዟል) ፡፡

49. ስለጉዳዩ የኢንተርፕራይዙ የበላይ ኃላፊዎች በቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ ላይ በሰጡት መልስ ኢንተርፕራይዙ ሲቋቋም የተለያዩ አገልግሎቶችን ማከናወን እንደሚችል ከዚህም መካከል የማማከር አገልግሎት አንዱ መሆኑን እና አማካሪዎቹ የሀዋሳ ዩኒቨርስቲ የቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት መምህራኖች መሆናቸውን እና በማማከር አገልግሎት ላይ ከኢንተርፕራይዙ ጋር በጋራ ለመስራት በእነሱ ተነሳሽነት ሀሳቡ እንደመጣ እና በዛ መሰረት የሙያ ፈቃድ፣ የብቃት ማረጋገጫ እና የትምህርት ማስረጃቸውን መሰረት በማድረግ በኢንተርፕራይዙ በኩል የንግድ ፈቃድ የወጣ መሆኑን፤ እና ስራዎች የሚመጡት የአማካሪዎቹን ሙያና ልምድ መሰረት አድረጎ መሆኑን፤ ነገር ግን በኢንተርፕራይዙ መዋቅር ላይ የማማከር አገልግሎት አለመኖሩን፤ በተጨማሪም የማማከር ስራዎች ከተጠናቀቁ በኋላ ኢንተርፕራይዙ ከትርፉ 15% ብቻ የሚያገኝ መሆኑን፣ እነዚህ ስራዎች ሲሰሩ ኢንተርፕራይዙ በአዲሱ የገቢ ማስገኛ ደንብና መመሪያ መሰረት ባለመስራቱ መሆኑን እና ለወደፊት በአዲሱ መዋቅር ላይ የማማከር አገልግሎት በኢንተርፕራይዙ ስር እንደ አንድ ዩኒት (unit) ተጠሪ ሆኖ እንደሚቋቋም፤ በተጨማሪም በማማከር አገልግሎት ላይ የውጭ

አበል ተመን 850 ብር የሆነው አማካሪ ማህበሮቹ ሲደራጁ ይዘውት የመጡት እንደሆነ እና በዛ መሰረት ክፍያ እንደሚፈጸም ገልጸዋል፡፡

50. በተጨማሪም በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት መልስ

- ዩኒቨርሲቲው ኢንተርፕራይዙን ሲመሰርት የማማከር አገልግሎት ስራዎች በኢንተርፕራይዙ መሰራት እንዳለበት በመመስረቻ ጽሁፍና መተዳደሪያ ደንብ ላይ አጽድቆ ለማማከር አገልግሎት ማህበሩ የተሰጠ መሆኑን፤
- ዩኒቨርሲቲ መምህራን የማማከር አገልግሎት ሥራዎችን እንዲሰሩ የወሰነበት ምክንያት በሙያቸው ለህብረተሰቡ አገልግሎት እንዲሰጡና የሚያስተምሩትን ትምህርት በተግባር በማስደገፍ ለሀገሪቱ ልማት ተጨማሪ እሴት እንዲጨምሩና በቅርበት በሙያቸው እያገለገሉ ተማሪዎቻቸውን እንዲያስተምሩ መሆኑን፤
- ኢንተርፕራይዙ በማማከር አገልግሎት ላይ ለሚሰማሩ ባለሙያዎች የክፍያ ተመን መነሻ ያደረገ በገንዘብ ሚኒስቴር ጥቅምት 24/2013 ቁጥር የ/ተ/መ/2/16/671 እና በቀን 20/07/2011 ዓ.ም ቁጥር 7/ኢ/113/56 ክፍል ሁለት/ገጽ 3 ለፕሮጀክቶች የተፈቀደውን አሰራር መሆኑን ፤
- ህጋዊነቱን በተመለከተ ኢንተርፕራይዙ ህጋዊ ተቋም ስለሆነ በዚህ ተቋም ውስጥ መምህራን ሥራን እንዲሰሩ እና በሌላ አደረጃጀት እንዲመጡ ያልተደረገበት ምክንያት መምህራኑ በዩኒቨርሲቲው በቋሚነት የተቀጠሩ በመሆናቸው መሆኑን፤
- በተጨማሪም በነጋሪት ጋዜጣ 9ኛ ዓመት ቁጥር 72 /1995 ዓ.ም በወጣው አዋጅ መምህራን ምርምር ሥራዎችን ከየትኛም ተቋም ጋር የመስራት ነጻነት እንዳላቸው፤
- ባለሙያዎቹ ጊዜያቸን ጉልበታቸንና ዕውቀታቸን ባዋሉት ልክ 85% ለሥራው የወጣ ወጪ እና ለላቸው በውሉ መሰረት የተከፈላቸው መሆኑን

ገልጸዋል፡፡

51. በኦዲቱ የመውጫ ስብሰባ ወቅት በማማከር አገልግሎት ላይ የሚሳተፉ የሃና ሃ ነክ ባለሙያዎች በሰጡት መልስ የዩኒቨርስቲው መምህራኖች በኢንተርፕራይዙ የማማከር አገልግሎት ላይ ሲሳተፉ እንደ አንድ አሃድ (unit) እንጂ ማህበር አለመሆናቸውን በመሆኑም ከተለያዩ ተቋማት ጋር በኢንተርፕራይዙ በኩል ውል በመዋዋል የማማከር ስራዎችን የሚሰሩ መሆኑን እንዲሁም በአለም ባንክ በሚደገፉ ፈንድ የሚሰሩ ስራዎችን ጭምር እንደሚሰሩ እና ክፍያዎችም በነሱ አሰራር የሚከፈል መሆኑን ገልጸዋል፡፡ እና መምህራኖቹ የተዋቀሩት ፈቃደኛ ሆነ አስፈላጊውን የሙያ ፈቃድ

ባወጡ ወይም ባላቸው ሙያ ሲሆን እንደ አንድ አሃድ ስራዎችን ለመደገፍ ከኢንተርፕራይዙ ጋር የመግባቢያ ሰነድ በመፈራረም የሚሰሩ መሆኑን እንዲሁም ከዩኒቨርስቲ ራዕይ ጋር የሚጣጣሙ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡ በተጨማሪም የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ መምህራኖች ፕሮጀክቶችን በመጻጻፍ በተዋረድም የቴክኒክና የፋይናንሻል ዕቅዶችን በማዘጋጀት የማማከር አሀዱን የሚደግፉ መሆኑን፤ ከጉርሻ አከፋፈል ጋር በተያያዘ አከፋፈሉ ግለሰቦችን ለመጥቀም ሳይሆን አብዛኞቹ ስራዎች የተሰሩት ሀገራዊ የጸጥታ ችግር በከፍተኛ ደረጃ በነበረባቸው ቦታዎች መሆኑን፤ በመስክ ላይ ከፍተኛ ተግዳሮትን ያሳለፉ በመሆናቸው መሆኑን፤ የበረሃ አበል ሳይከፈላቸው በረሃማ እና ርቀት ያላቸው ስፍራዎች ላይ በመሰማራታቸው መሆኑን እና ስራዎቹ የህይወት መስዋትነትን ጭምር እንደሚያስከትሉ ገልጸዋል፡፡ የውሎ አበል ተመንን በተመለከተ ሁሉም ስራዎች ፕሮጀክቶች ሲሆኑ፤ ክፍያዎቹም የተከፈሉበት ተመን በግልጽ በየፕሮጅክቶቹ ዝርዝር ከደንበኛ(ከአሰሪው) ጋር በመስማማት መሆኑን ገልጸዋል፡፡

52. የኢንርፕራይዙ ኃላፊዎች እና የዩኒቨርሲቲ ባለሙያዎቹ ይህን ምላሽ ቢሰጡም

- ከኢንተርፕራይዙ ጋር በማማከር አገልግሎት ላይ ለመሳተፍ ውል የተዋዋሉበት ሰነድ ማስረጃ ማህበር ስለመሆናቸው የሚገልጽ በመሆኑ እና የሙያ ፈቃድ እንደ ንግድ ፈቃድ ስለሚያገለግል ኢንተርፕራይዙ ህጋዊ ሰውነት ከሌለ ማህበር ጋር የመግባቢያ ሰነድ እና ውል በመግባቱ፤
- የዩኒቨርሲቲን መምህራን እና ተመራማሪዎች እንዴት መጠቀም እንዳለበት እንዲሁም የኮንትራት አሰጣጥ እና የክፍያ አተማመን ህጋዊ የአሰራር ስርዓት በማውጣትና በቦርድ በማጸደቅ ተግባራዊ ማድረግ ስለነበረበት፣
- አማካሪ ማህበራት የተባሉትም እንደማህበር ተደራጅተው ስለመቋቋማቸው ማስረጃ ያልቀረበ እና ሕጋዊ ሰውነት ከሌለ አካል ጋር ውል መፈጸም ተጠያቂነትን ለማስፈን ስለማያስችል፤
- በተጨማሪም ማንኛውም የክፍያ ተመን ሆነ ማበረታቻ ክፍያ በዩኒቨርሲቲው የሥራ አመራር ቦርድ ያልጸደቀ በመሆኑ እንዲሁም የማመከር ማህበሮቹ በማማከር አገልግሎት ላይ ለሚሳተፉ ባለሙያዎች የአበል እና የጉርሻ ክፍያ ተመን ኢንተርፕራይዙ በሚጠቀምበት የመንግስት የውሎ አበል መሆን ስለነበረበት፤ ነገር ግን ማህበሮቹ በ2013 ዓ.ም ገንዘ[illegible] ባወጣው በልማት ድርጅቶች ድጋፍ ለሚተገበሩ ፕሮግራሞችና [illegible]

የክፍያ ተመን መሰረት በመሆኑ ይህም ከኢንተርፕራይዙ አሰራር ጋር የማይጣጣም እና በቦርድ ያልጸደቀ ስለሆነ

የተሰጠን መልስ አልተቀበልነም፡፡

53. ኢንተርፕራይዙ በማማከር አገልግሎት ላይ የዩኒቨርሲቲን ባለሙያዎች በጊዜያዊነት ለመጠቀምና ምን አይነት የክፍያ ሥርዓት መፈጸም እንዳለበት ግልጽ የሆነ መስፈርት ባለማጣቱና በቦርድ አለመጸደቁ ከሚሰሩ ስራዎች የሚያገኘው ትርፍ ዝቅተኛ እንዲሆን እና ከሌሎች ድርጅቶች ጋር ተወዳዳሪና ትርፋማ እንዳይሆን እንዳደረገ፣ በሥራ አመራር ቦርድ ያልጸደቀ ክፍያ መክፈልም ለህገወጥ አሰራር ምቹ ሁኔታ የሚፈጥርና ተጠያቂነት እንዳይጠናከር ያደርጋል፡፡

የኢንተርፕራይዙን የአገልግሎት አሰጣጥ ቅሬታዎች የሚስተናግዱበት ስርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ፤

54. ኢንተርፕራይዙ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 456/2012 ዓ.ም አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 3 መሰረት የአገልግሎት አሰጣጡን በሚመለከት የሚቀርቡ ቅሬታዎች የሚስተናገዱበት ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

55. ይሁን እንጂ የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ የገቢ ማመንጫ ኢንተርፕራይዝ የአገልግሎት አሰጣጥን በሚመለከት የሚቀርቡ ቅሬታዎች የሚስተናገዱበት ስርዓት እንዳልተዘረጋ እና የሥራ አመራር ቦርዱ ስርዓቱ ስለመዘርጋቱ የማይከታተል መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

56. ስለጉዳዩ የኢንተርፕራይዙ የበላይ ኃላፊ በቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ፣ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ እና በመውጫ ስብሰባ ወቅት በሰጡት መልስ ከ2012 ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ አሰራር ለቦርድ ተጠሪ ሆኖ ባለመቋቋሙ መሆኑን እና የቅሬታ ማስተናገጃ መኖር እንዳለበት እንዲሁም ደንቡን መነሻ አድርጎ መዋቅሩ ሲጸድቅ ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ እንደሚደረግ ገልጸዋል፡፡

57. በተጨማሪም በተላከላቸው የኦዲት ረቂቅ ሪፖርት በሰጡት መልስ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 456/2012 ዓ.ም በተደነገገ መሰረት የተዘረጋ የቅሬታ ማስተናገጃ አሰራር ስርዓት ባይኖርም በነባሩ መዋቅራቸው ላይ በሰው ሀብት መመሪያ አንቀጽ 7 ከሰራተኞች ዲሲፕሊን ጉዳይ ጋር የተያያዙ ቅሬታዎች ሲኖሩ የተቋቋሙ ኮሚቴዎች አጣርተው ምላሽ እንደሚሰጡ እና የተቋቋሙትን ኮሚቴዎች ማስረጃ መላካቸውን ገልጸዋል፡፡

58. የኢንተርፕራይዙ የበላይ ኃላፊዎች ይህን ይበሉ እንጂ በኢንተርፕራዙ የሰው ኃብት መመሪያ መሰረት በ2015 ዓ.ም የተመረጡት የቅሬታ አጣሪ ኮሚቴዎችን ዝርዝር ለቦርድ በማቅረብ እና ውሳኔ እንዲሰጥበት ማድረግ ስለነበረበት እንዲሁም ኮሚቴዎቹ ዘግይተው የተቋቋሙ በመሆኑ የድርጅቱ የሰው ኃብት መመሪያ ከወጣበት ዕለት ጀምሮ መቋቋም ስለነበረባቸው የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

59. ኢንተርፕራይዙ የቅሬታ ማስተናገጃ ስርዓት ባለመዘርጋቱ አገልግሎት አሰጣጡ ምን ደረጃ ላይ እንዳለ እንዳይታወቅ እንዲሁም የሚያቀርባቸው ምርቶች ጥራታቸው የተጠበቀ ለማድረግ እና ለማሻሻል አስቸጋሪ ያደርገዋል፡፡

የኢንተርፕራይዙ የስራ ፕሮግራምና፣ በጀት በቦርድ መጽደቁን እና በየጊዜ አፈጻጸሙ መገምገሙን በተመለከተ፤

60. ኢንተርፕራይዙ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የገቢ ማስገኛ ድርጅት ደንብ ቁጥር 456/2012 ዓ.ም አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 4 መሰረት የስራ ፕሮግራሙን እና በጀቱን ለቦርድ አቅርቦ ሊያጸድቅ ይገባል፡፡ በተጨማሪም የጸደቀ ፕሮግራምና በጀት አፈጻጸም በየጊዜ ለሥራ አመራር ቦርድ እየቀረበ ሊገመገም ይገባል፡፡

61. ይሁን እንጂ፡-

- ኢንተርፕራይዙ ከ2012 ዓ.ም ጀምሮ 2013 ዓ.ም፣ 2014 ዓ.ም እና የ2015 ዓ.ም አመታዊ የስራ ዕቅዱን፣ ፕሮግራሙን እና በጀቱን ዩኒቨርሲቲውን በበላይነት ለሚያስተዳድረው ቦርድ ቀርቦ ያልጸደቀ መሆኑን፤
- ኢንተርፕራይዙ ከ2012 ዓ.ም ጀምሮ የስራ አፈጻጸሙን እና የሂሳብ ሪፖርቶቹን አዘጋጅቶ ለቦርድ ያላቀረበ መሆኑን፤

በኦዲት ወቅት ከተከለሱ ሰነዶች እና ከቀረቡ ቃለ-መጠይቆች ለማወቅ ተችሏል፡፡

62. ስለጉዳዩ የኢንተርፕራይዙ የበላይ ኃላፊ በቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ ፣ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ፣ በመውጫ ስብሰባ ወቅት እና በተላከላቸው ረቂቅ የኦዲት ሪፖርት ላይ በሰጡት መልስ ኢንተርፕራይዙ በአዲሱ የገቢ ማስገኛ ደንብና መመሪያ ባለመቋቋሙ ከቦርድ ጋር እንደማይገናኙ እና ደንቡን መነሻ አድርጎ የኢንተርፕራይዙ መዋቅር ሲጸድቅ ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ እንደሚደረግ ገልጸዋል፡፡

63. ኢንተርፕራይዙ ፕሮግራሙን፣ በጀቱን ለቦርድ እያቀረበ ካላጸደቀ እና አ
በሥራ አመራር ቦርድ በየጊዜ አለመገምገሙ ኢንተርፕራይዙ የተቋቋመበ

እያሳካ መሆኑን ማረጋገጥ እንዳይቻል፣ ለብልሹ አሰራር እና ለህገወጥነት በር ይከፍታል፡፡

2.2 የገቢ ማመንጫ ኢንተርፕራይዙ የገቢ ማመንጫ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የተዘረጋ ሥርዓት ኢኮኖሚያዊ ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መልኩ ማሳደጉን መገምገም፤

የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ገቢ ማመንጫ ኢንተርፕራይዝ የግዥ እቅድ አዘጋጅቶ በቦርድ ያጸደቀ መሆኑን በተመለከተ፤

64. ኢንተርፕራይዙ በግዥ መመሪያው መሰረት የግዥ ዕቅድ አዘጋጅቶ ለቦርድ ሊያቀርብ እና ሊያጸድቅ ይገባል፡፡

65. ኢንተርፕራይዙ የመንግስትን የግዥ ሥርዓት ተከትሎ ግዥ እንደሚፈጽም በኦዲቱ ወቅት ኃላፊዎቹ ገልጸዋል፡፡ ይሁን እንጂ፡-

- ኢንተርፕራይዙ ከ2012 ዓ.ም ጀምሮ የግዥ ዕቅድ አዘጋጅቶ ለቦርድ በማቅረብ ያላጸደቀ መሆኑን፤
- ኢንተርፕራይዙ በግዥ መመሪያ መሰረት የግዥ አጽዳቂ ኮሚቴ በማቋቋም የግዥ ዕቅድ በኮሚቴ እንዲረጋገጥ የማይደረግ መሆኑን፤
- ለማዕከላት በሥራ ላይ ያለ የግዥ መመሪያ ያልደረሰ መሆኑን በናሙና የታዩ ማዕከላት መግለጻቸውን፤
- የሚፈጸሙ ግዥዎች በዕቅድ የተመሰረቱ አለመሆኑን እና ተመሳሳይ ስራ የሚከናወንባቸው የንግድ ማዕከላት የተለያየ የግዥ ዕቅድ የሚቀርብ መሆኑን፤

በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ሰነዶች እና ከቀረቡ ቃለ-መጠይቆች ለማወቅ ተችሏል፡፡

66. ስለጉዳዩ የኢንተርፕራይዙ የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው በመውጫ ስብሰባ ወቅት እና በተላከላቸው ረቂቅ ሪፖርት ላይ በሰጡት ምላሽ ኢንተርፕራይዙ አራት ማዕከላት እንዳለው እና የሁሉም ማዕከላት የግዥ እና የፋይናንስ ስራ በዋናው ጽ/ቤት የሚሰራ መሆኑን እንዲሁም የግዥ ዕቅድ ለቦርድ የማይቀርበ ኢንተርፕራይዙ ከቦርድ ጋር ግንኙነት ስለሌለ መሆኑን፤ በተጨማሪም በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት መልስ ኢንተርፕራይዙ በዋና ጽ/ቤት ደረጃ የግዥ አጽዳቂ ኮሚቴ ያለ መሆኑ እና በማዕከላት ደረጃ የሚፈጸም ግዥ እንደሌለ ገልጸዋል፡፡ በተጨማሪም የኢንተርፕራይዙ የበላይ ኃላፊ ኢንተርፕራይዙ የግዥ ዕቅድ ለቦርድ የማይቀርበ ኢንተርፕራይዙ ከቦርድ ስር ባለ

ግንኙነት ስለሌለው መሆኑን እና በአዲሱ መዋቅር መሰረት ከስራ አመራር ቦርድ ወይም ቦርዱ ከሚወክላቸው ኃላፊዎች ጋር በቀጣይ አጠናክሮ እንደሚሰሩ ገልጸዋል፡፡

67. የኢንተርፕራይዙ የበላይ ኃላፊ ይህን ይበሉ እንጂ የግዥ አጽዳቂ ኮሚቴ ስለመቋቋሙ እና የማዕከላት የግዥ ዕቅድ በኮሚቴ እየተገመገመ የጸደቀ የግዥ ዕቅድ ለማዕከላት እንዲደርስ ስለመደረጉ የሚያሳይ ማስረጃ ባለመቅረቡ እንዲሁም የኢንተርፕራይዙ ማዕከላት በመመሪያው መሰረት የግዥ ዕቅድ ለማዘጋጀት እንዲረዳቸው የግዥ መመሪያ እንዲደርሳቸው ባለመደረጉ እና አጠቃላይ የግዥ ዕቅድ በቦርድ እንዲጸድቅ ባለመደረጉ የተሰጠው ምላሽ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

68. ኢንተርፕራይዙ የግዥ ዕቅዱን ለቦርድ አቅርቦ ካላጸደቀ የሚፈጸሙ ግዥዎች ከዕቅድ ጋር እንዳይናበቡ፣ በዕቅዱ መሰረት ግዥ መፈጸሙ እንዳይረጋገጥ እንዲሁም አማራጭ ሊኖራቸው የሚችሉ የግዥ ሁኔታዎች በቦርድ ውሳኔ እንዳይሰጥባቸው ከማድረጉም በላይ ህገወጥነት በማስፈን ደረጃቸውን ያልጠበቁ እቃዎች እንዲገዙ እና የኢንተርፕራይዙ ሀብትን አላግባብ እንዲባክን ያደርጋል፡፡

በኢንተርፕራይዙ ለሚቀርቡ አገልግሎቶች እና ምርቶች ክፍያዎች በወቅቱ መሰብሰባቸውን በተመለከተ፣

69. የገቢ ማመንጫ ኢንተርፕራይዙ ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች እና ምርቶች ክፍያዎችን በወቅቱ ሊሰበስብ ይገባል፡፡

70. ይሁን እንጂ፡-

- ኢንተርፕራይዙ ላቀረባቸው ምርቶች/አገልግሎቶች ክፍያዎችን እና ሌሎች ተሰብሳቢዎችን በውሉ መሰረት እና በወቅቱ እንደማይሰበስብ ታውቋል፡፡ ለማሳያም፣
  - ኢንተርፕራይዙ በቀን 27/08/2013 ዓ.ም 12,300,000 ብር የሚያወጣ የተማሪዎች ተደራራቢ አልጋና ሎከር ለማቅረብ ከጂንካ ዩኒቨርስቲ ጋር ውል ተዋውሎ በውሉ ላይ ኢንተርፕራይዙ ስራውን ማጠናቀቅ ያለበት በግንቦት 27/2013 ዓ.ም የተገለጸ ሲሆን በውሉ መሰረት ኢንተርፕራይዙ ስራውን አጠናቆ ለዩኒቨርስቲው ያስረከበ ሲሆን ነገር ግን ክፍያው በጂንካ ዩኒቨርስቲ በኩል ስለመፈጸሙ ማስረጃ ተጠይቆ ያልቀረበ መሆኑ፣
  - ኢንተርፕራይዙ በ2012 በጀት ዓመት ለገቢዎች ሚኒስቴር ታክስ ለማሳወቅ ካዘጋጀ ሪፖርት ላይ ለማወቅ እንደተቻለ ያልተሰበሰበ ብር 28,074,759.99 መኖሩን፣

- ኢንተርፕራይዙ በ2013 በጀት ዓመት ለገቢዎች ሚኒስቴር ታክስ ለማሳወቅ ካዘጋጀ ሪፖርት ላይ ለማወቅ እንደተቻለ ያልተሰበሰበ ብር 35,727,876.94 መኖሩን፤
- ኢንተርፕራይዙ በ2014 በጀት ዓመት ለገቢዎች ሚኒስቴር ታክስ ለማሳወቅ ካዘጋጀ ሪፖርት ላይ ለማወቅ እንደተቻለው ያልተሰበሰበ ብር 56,468,150.30 መኖሩን፤



- በተጨማሪም በ2009 ዓ.ም በወቅቱ የነበረ የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ገቢ ማመንጫ ኢንተርፕራይዝ ስራ አመራር ቦርድ በቀን 18/05/2009 ዓ.ም በስብሰባ ላይ በገቢ ማመንጫ ኢንተርፕራይዙ ምስረታ ወቅት በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ሀዋሳ ቅርንጫፍ በአካውንት ቁጥር 1000131104441 ለገቢ ማመንጫ ፕሮጀክቶች ማስፋፊያ በሪዘርቭ ሂሳብ የተቀመጠ ብር 25,000,000 ወጪ ተደርጎ በጨረታ ውድድር አሸናፊነት በአዲስ አበባ ከተማ ሊገዛ ለታቀደ የእንግዳ ማረፊያ ቤት ግዥ አገልግሎት እንዲውል እንዲደረግ፣ የተጨማሪ እሴት ታክስን ጨምሮ ከላይ በውይይቱ ከተጠቀሰ ብር በተጨማሪ 10,075,000 ብር ከኢንተርፕራይዙ መንቀሳቀሻ ካፒታል ላይ ወጪ ሆኖ አጠቃላይ 35,075,000 ብር ከኢንተርፕራይዙ አካውንት ወጪ ሆኖ እንዲከፈል፣ እና ከኢንተርፕራይዙ መንቀሳቀሻ ካፒታል ላይ ወጪ የሆነው ገንዘብ ዩኒቨርሲቲ ከተለያየ ምንጭ ከሚሰበስበ ገንዘብ እንዲተካ እንዲደረግ፤ የተወሰነ እና ገንዘቡ ወጪ ተደርጎ ተከፍሏል:: በቦርዱ ውሳኔ መሰረት ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ለኢንተርፕራይዙ ገንዘቡ እንዲመለስ ያልተደረገ መሆኑን፣

ከተከለሱ ሰነዶች እና ከቀረቡ ቃለ-መጠይቆች ለማወቅ ተችሏል፡፡

71. ስለጉዳዩ የኢንተርፕራይዙ ኃላፊዎች በቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ ላይ በሰጡት መልስ ኢንተርፕራይዙ አገልግሎቶችን እና ምርቶችን ለደንበኞቹ በዱቤ የሚሰጥ መሆኑን እና ተጠቃሚዎቹ ክፍያውን በወቅቱ እንደማይከፍሉ በዚህም ኢንተርፕራይዙ ክፍያ በወቅቱ እንዲከፍሉ ደብዳቤ ቢጽፍም ተጠቃሚዎቹ በወቅቱ ለመክፈል ፈቃደኛ ባለመሆናቸው መሆኑን፤ የአዲስ አበባ እንግዳ ቤት ማረፊያ ቤት ግዥን በተመለከተ በወቅቱ ቤቱ ለኢንተርፕራይዙ ተብሎ ሊገዛ እንደነበር እና በመጨረሻ በዩኒቨርስቲ ማኔጅመንት የሀሳብ ልዩነት ተፈጥሮ ቤቱ ለዩኒቨርስቲ እንዲሆን የተደረገ መሆኑን፤ በተጨማሪም ከኢንተርፕራይዙ አካውንት ላይ ተቀንሶ ለቤቱ ግዥ የዋለን ገንዘብ እንዲመለስ ያልተደረገ ድርጅቱ ከሚያገኘው ትርፍ ላይ ለዩኒቨርስቲው ስላልሰጠው መሆኑን ገልጸዋል፡፡

72. በተጨማሪም በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ እና በተላከላቸው ረቂቅ ሪፖርት ላይ በሰጡት መልስ ከላይ የተጠቀሱት የኢንተርፕራይዙ ተሰብሳቢ ሂሳቦች የገንዘብ መጠን ድርጅቱ በአሁን ጊዜ የሚሰበሰበ ሳይሆን ተሰብስቦ ገቢ የተደረገ መሆኑን እና ችግሩ በአመዘጋገብ ስህተት ላይ የነበረ መሆኑን እና ችግሩ ተቀርፎ መስተካከሉን እንዲሁም ዩኒቨርስቲ ለአዲስ አበባ ቤት ግዥ የተጠቀመን የኢንተርፕራይዙን ገንዘብ ኢንተርፕራይዙ እንደገና በአዲሱ ደንብ መሰረት ሲቋቋም በጊዜው ታሳቢ ተደርጎ ክፍያ የሚሸፈን መሆኑን ገልጸዋል፡፡ በመውጫ ስብሰባ ወቅት ደግሞ የዩኒቨርሲቲው ፕሬዝዳንት እና የኢንተርፕራይዙ ኃላፊ በሰጡት ምላሽ ግኝቱ እንደተቀበሉት እና ወደፊት እንደሚያስተካክሉ ገልጸዋል፡፡

73. የኢንተርፕራይዙ የበላይ ኃላፊ ይህን ቢሉም ከ2012 ዓ.ም እስከ 2014 በጀት ዓመት ድረስ በየአመቱ ኢንተርፕራይዙ ተሰብሳቢ ሂሳብ ብሎ ለገቢዎች ሚኒስቴር ያሳወቀ ሲሆን ተሰብሳቢ ሂሳቡ በየበጀት አመቱ ተጠቃሎ ስለመሰብሰቡ እና ገቢ ስለመደረጉ የሚያሳይ የገቢ ሂሳብ መግለጫ ማስረጃ ባለመቅረቡ እንዲሁም ከኢንተርፕራይዙ ካፒታል ላይ ለቤት ግዥ የተቀነሰው ብር 35,075,000 በቦርዱ ውሳኔ መሰረት ለኢንተርፕራይዙ ተመላሽ መደረግ ስለነበረበት የተሰጠውን መልስ አልተቀበልነውም፡፡

74. ኢንተርፕራይዙ ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች እና ምርቶች ክፍያዎችን በወቅቱ ባለመሰብሰቡ የድርጅቱ ተሰብሳቢ ሂሳብ እንዲጨምር እና የስራ መንቀሳቀሻ የሚሆን የካሽ ገንዘብ ዕጥረት እንዲያጋጥም ከማድረጉም በላይ ኢንተርፕራይዙ አዲስ የገቢ

ማመንጫ ዘርፎችን ለመክፈት እና ለማስፋፊት የካፒታል እጥረት እንዲያጋጥም አድርጓል፡፡

ኢንተርፕራይዙ የውስጥ ኦዲት ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረጉን በተመለከተ፡-

75. ኢንተርፕራይዙ የውስጥ ኦዲት አደረጃጀት በመፍጠር እና በየጊዜ ኦዲት እያደረገ ሪፖርቱን ለኢንተርፕራይዙ ማኔጅመንት እና ለቦርድ ሊያቀርብ ይገባል፡፡

76. ይሁን እንጂ ኢንተርፕራይዙ ከ2012 ዓ.ም ጀምሮ የውስጥ ኦዲቱ ማዕከላቱንም ሆነ የፋይናንስ መግለጫዎቹን ኦዲት እያደረገ ለቦርድ ያላቀረበ መሆኑን እንዲሁም በኢንተርፕራይዙ ስር ባሉ ማዕከላት የሚሰሩ ስራዎችን በየግዜ ኦዲት እየተደረገ የኦዲት ሪፖርት እንደማይቀርብ ከተከለሱ ሰነዶች እና ከቀረቡ ቃለ-መጠይቆች ለማወቅ ተችሏል፡፡

77. ስለጉዳዩ የኢንተርፕራይዙ የበላይ ኃላፊዎች በቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ ፣ በነበራዊ ሁኔታ መግለጫ ፣ በመውጫ ስብሰባ ወቅት እና በተላከላቸው ረቂቅ የኦዲት ሪፖርት ላይ በሰጡት መልስ የቀረበውን ግኝት ተቀብለው እንደሚያስተካክሉ፤ በኢንተርፕራይዙ የውስጥ ኦዲት ባለሙያ አንድ ብቻ መሆኑን ይህም የሆነው በመዋቅሩ መሰረት ተወዳዳሪ የሆነ ባለሙያ ለመቅጠር ስለማይጋብዝ መሆኑ እና በአዲሱ መዋቅር ላይ እንዲሻሻል የተደረገ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

78. የኢንተርፕራይዙ የበላይ ኃላፊ ይህንን ቢሉም ባለ የሰው ኃይል መሰረት የተወሰነ ሥራ መስራት ስለነበረባቸው እና አላሰራው ያለው መዋቅር እንዲሻሻል ማድረግ ስለነበረባቸው የተሰጠውን መልስ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

79. ኢንተርፕራይዙ በየጊዜ የውስጥ ኦዲት እያደረገ ሪፖርት ለቦርድ ባለማቅረቡ በኢንተርፕራይዙ በማዕከላት የሚሰሩ ስራዎች በትክክል እንዳይታወቁ እና ንብረቶች በአግባቡ እንዳይያዙ እንዲሁም የአሰራር ክፍተት እንዲያጋጥም አድርጓል፡፡

ኢንተርፕራይዙ በስሩ ላሉ የስራ ክፍሎች ስልጠና መስጠቱን በተመለከተ፤

80. የገቢ ማመንጫ ኢንተርፕራይዙ በስሩ ባሉት የስራ ክፍሎች (business units) ለሚገኙ ሰራተኞች የአቅም ክፍተት በመለየት፣ አስፈላጊውን የሙያ እና ክህሎት ስልጠና ሊሰጥ ይገባል፡፡

81. ይሁን እንጂ ኢንተርፕራይዙ በስሩ ባሉት የስራ ማዕከላት የሚገኙ ሰራተኞችን የአቅም ክፍተት በየዘርፉ በማጥናት እና በመለየት አስፈላጊውን የሙያና የክህሎት ስልጠና

ያልሰጠ መሆኑን እንዲሁም ኢንተርፕራይዙ በ2012፣ 2013 እና 2014 በጀት አመታት ለስልጠና ወጪ ተብሎ በየአመቱ 50,000 (ሀምሳ ሺ) ብር ያቀደ ሲሆን በዕቅዱ መሰረት ስልጠናው በሁሉም በጀት አመታት ያልተሰጠ መሆኑን ከተከለሱ ሰነዶች እና ከቀረቡ ቃለ-መጠይቆች ለማወቅ ተችሏል፡፡

82. የኢንተርፕራይዙ የበላይ ኃላፊ በተላከላቸው የነበራዊ ሁኔታ መግለጫ ፣ በመውጫ ስብሰባ ወቅት እና በረቂቅ ሪፖርት ላይ በሰጡት መልስ ዋናን ስልጠና ለማዘጋጀት መዋቅር ጸድቆ በየቦታው የሚመደቡ ሰራተኞችን ለማሰልጠን እየጠበቁ መሆኑን እና ግኝቱን ተቀብለው ወደፊት እንደሚያስተካክሉ ገልጸዋል ፡፡

83. ኢንተርፕራይዙ ከ2012 ዓ.ም ጀምሮ በየአመቱ ለስልጠና ተብሎ በጀት የያዘ በመሆኑ እና በዕቅዱ መሰረት ስልጠናን ማከናወን ስለነበረበት የተሰጠን ምላሽ አልተቀበልነውም፡፡

84. ኢንተርፕራዙ በዕቅዱ መሰረት ስልጠና አለመስጠቱ የአሰራር ክፍተት እንዲፈጠር እና ሰራተኞች የስራ ክህሎታቸን እዳያጎለብቱ እንዲሁም ከአዳዲስ አሰራር ጋር እንዳይላመዱ አድርጓል፡፡

ኢንተርፕራይዙ የገቢ ማመንጫ ዘርፎችን ማስፋፋቱን እና ማጠናከሩን በተመለከተ፤

85. ኢንተርፕራይዙ የገቢ ማመንጫ ዘርፎችን በማጠናከር እና በማስፋፋት ትርፋማነቱን ሊያሳድግ ይገባል፡፡

86. ይሁን እንጂ፡-

- ኢንተርፕራይዙ የገቢ ማመንጫ ዘርፎችን ያላስፋፋ መሆኑ እንዲሁም የድርጅቱን ትርፋማነት እንዲያሳድግ/እንዲጨምር ያልተደረገ መሆኑ እንዲሁም በየጊዜው ለኪሳራ እየተዳረገ መሆኑ፤
- በእርሻ ማዕከሉ የወተት ምርት መጠን በከፍተኛ ሁኔታ የቀነሰ መሆኑን በዚህም በ2012 ዓ.ም ከአንድ ላም በቀን በአማካይ ሲገኝ ከነበረ 8.9 ሊትር ወተት በመቀነስ ወደ 4.00 ሊትር ያህል የቀነሰ መሆኑን ፤
- በእርባታ ማዕከሉ የከብቶች የምርታማነት ማነስ በዚህም የሚታለቡ ላሞች ቁጥር በየጊዜው እየቀነሰ መምጣቱ በ2013 ዓ.ም 37 የሚታለቡ ላሞች ሲኖሩ በ2014 ዓ.ም 17 የሚታለቡ ላሞች እና በ2015 ዓ.ም 15 የሚታለቡ ላሞች ብቻ መኖራቸው



- በወተት ማቀነባበር ስራ ላይ የጥሬ ወተት አቅርቦት ማነስ፣ የአንዳንድ የፋብሪካ መለዋወጫዎች በቅርብ አለመገኘት፣ የምርት ሂደቱ አመራር ልምድ እና ክህሎት ማነስ ችግሮች መኖራቸውን፣
- በወተት ማቀነባበሪያ ማዕከል በቀን ማምረት የሚችለ 2000 ሊትር ወተት ማቀነባበር የሚችል ሲሆን አሁን ባለው የምርት መጠን ከአቅም በታች ከ500 እስከ 600 ሊትር ብቻ እያመረተ መሆኑን፤
- ኢንተርፕራይዙ በ2012 ዓ.ም ዕቅድ አፈጻጸም ሪፓርት ላይ ከሆቴል አገልግሎት ያገኘው አጠቃላይ ገቢ ብር 4,936,612.42 (አራት ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ሰላሳ ስድስት ሺ ስድስት መቶ አስራ ሁለት ብር ከ 42/100) ሲሆን ጠቅላላ ወጪ ደግሞ ብር 5,310,905.17 (አምስት ሚሊዮን ሶስት መቶ አስር ሺ ዘጠኝ መቶ አምስት ብር ከ 17/100) በመሆኑ በበጀት ዓመቱ ለብር 374,292.75(ሶስት መቶ ሰባ አራት ሺ ሁለት መቶ ዘጠና ሁለት ብር ከ75/100) ኪሳራ መዳረጉን፤
- ኢንተርፕራይዙ በ2013 ዓ.ም ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ላይ ከእርሻ ልማት ስራዎች ያገኘው አጠቃላይ ገቢ ብር 16,739,985.33 (አስራ ስድስት ሚሊዮን ሰባት መቶ ሰላሳ ዘጠኝ ሺ ዘጠኝ መቶ ሰማንያ አምስት ብር ከ33/100) ሲሆን ጠቅላላ ወጪ ደግሞ ብር 18,011,921.24 (አስራ ስምንት ሚሊዮን አስራ አንድ ሺ ዘጠኝ መቶ ሃያ አንድ ብር ከ 24/100) በመሆኑ በበጀት ዓመቱ ለብር 1,271,935.91 (አንድ ሚሊዮን ሁለት መቶ ሰባ አንድ ሺ ዘጠኝ መቶ ሰላሳ አምስት ብር ከ91/100) ኪሳራ መዳረጉን፤

- ከኢንተርፕራይዙ የ2014 ዓ.ም ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ላይ ከግብርና ከሊጅ የዕደ ጥበብ ማዕከል ያገኘው ጠቅላላ ገቢ 10,999,126.24(አስር ሚሊየን ዘጠኝ መቶ ዘጠና ዘጠኝ ሺ አንድ መቶ ሀያ ስድስት ብር ከ24/100) ሲሆን ጠቅላላ ወጪው ደግሞ 11,921,441.08(አስራ አንድ ሚሊየን ዘጠኝ መቶ ሀያ አንድ ሺ አራት መቶ አርባ አንድ ከ8/100) በመሆኑ በበጀት ዓመቱ ለ 922,314.84(ዘጠኝ መቶ ሀያ ሁለት ሺ ሶስት መቶ አስራ አራት ብር ከ84/100) ኪሳራ መዳረጉን፤
- ከኢንተርፕራይዙ የ2014 ዓ.ም ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ላይ ከእርሻ ማዕከል ያገኘው አጠቃላይ ገቢ 27,201,318.04(ሀያ ሰባት ሚሊየን ሁለት መቶ አንድ ሺ ሶስት መቶ አስራ ስምንት ብር ከ4/100) ሲሆን ጠቅላላ ወጪው ደግሞ 30,036,051.41(ሰላሳ ሚሊየን ሰላሳ ስድስት ሺ ሀምሳ አንድ ከ41/100) በመሆኑ በበጀት ዓመቱ ለ 2,834.733.37(ሁለት ሚሊየን ስምንት መቶ ሰላሳ አራት ሺህ ሶስት መቶ አስራ ስምንት ብር ከ37/100) ኪሳራ መዳረጉን፤

ከተከለሱ ሰነዶች እና ከቀረቡ ቃለ-መጠይቆች ለማወቅ ተችሏል፡፡

87. የኢንተርፕራይዙ የበላይ ኃላፊዎች በተላከላቸው ረቂቅ ሪፖርት ላይ በሰጡት ምላሽ ነባሮቹ የግዥና የፋይናንስ አሰራር መመሪያዎች በአካባቢና በአገር ደረጃ ካሉት ነባራዊ የገበያ ሁኔታዎች ጋር ብዙም ተወዳዳሪ እንዳይሆን ማነቆ መሆኑን እና ከፍተኛ የዋጋ ንረት መኖሩን ገልጸ ከነችግሩም ቢሆን የተሰጡትን አስተያየቶች ወስደ ወደ ስራ ለመግባት ጥረት እንደሚያደርጉ ገልጸዋል፡፡

88. ኢንተርፕራይዙ የገቢ ማመንጫ ዘርፎች እንዲስፋፉ እና እንዲጠናከሩ ባለማድረጉ ኢንተርፕራይዙ ተጨማሪ ገቢ እንዳያገኝ እንዲሁም ትርፋማነቱን እንዳያሳድግ ከማድረጉም ባለይ ለኪሳራ እንዲጋለጥ አድርጎታል፡፡

2.3 የገቢ ማመንጫ ኢንተርፕራይዙ የሀብት አስተዳደር፣ የገበያ ጥናት እና መረጃ አያያዝና ልውውጥ ስርዓት በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ መሆኑን መገምገም፣

ኢንተርፕራይዙ አዳዲስ ለሚከፍታቸው ገቢ ማመንጫ የአዋጭነት ጥናት ማድረጉን እና በቦርድ እንዲወሰን መደረጉን በተመለከተ፤

89. የገቢ ማመንጫ ኢንተርፕራይዙ አዳዲስ ለሚከፍታቸው የንግድ ስራዎች የአዋጭነት ጥናት ሊያደርግ እና የዋጋ ተመን በቦርድ ሊያጸድቅ ይገባል፡፡ በተጨማሪም የገቢ ማመንጫ ዘርፎች ሲጀምርም ሆነ ሲዘጋ ለቦርድ በማሳወቅ ፈቃድ ሊያገኝ ይገባል፡፡

90. ይሁን እንጂ፡-

- ➢ ኢንተርፕራይዙ አዳዲስ የንግድ ስራዎችን ለመጀመር የአዋጭነት ጥናት ያላደረገ መሆኑን፤
- ➢ ኢንተርፕራይዙ አዳዲስ የገቢ ማስገኛ ዘርፎችን ሲጀምርም ሆነ ሲዘጋ በቦርድ እንዲወሰን የማያደርግ መሆኑን፤
- ➢ በኢንተርፕራይዙ የፋይናንስ አሰራር መመሪያ 2008 ዓ.ም መሰረት ለሚሰጡ አገልግሎቶች እና ምርቶች የሽያጭ ዋጋ ተመን ውሳኔ በኢንተርፕራይዙ ስራ አመራር ቦርድ መወሰን እንዳለበት ቢገለጽም የዋጋ ተመኖች በቦርድ እየተወሰኑ አለመሆኑን፤
- ➢ በኢንተርፕራይዙ የሚወጡ ወጪዎች እና ግብዓቶችን የሚያጠና የኮስት አካንታት የሌለ መሆኑን፤
- ➢ ኢንተርፕራይዙ ካሉት የገቢ ማመንጫ ዘርፎች ውስጥ (የስጋ መሸጫ ልኳንዳ ቤት፣ የዶሮ እርባታ፣ የብሎኬት ምርት ሽያጭ) ስራ ተጀምረ ያቆሙ መሆኑን እና ለቦርድ በማሳወቅ ውሳኔ እንዲሰጥበት ያልተደረገ መሆኑን፤

በኦዲት ወቅት ከተከለሱ ሰነዶችና ከቀረቡ ቃለ-መጠይቆች ለማወቅ ተችሏል፡፡

91. ስለጉዳዩ የኢንተርፕራይዙ የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀ በሰጡት መልስ የስጋ ሽያጭ ተጀምሮ ያቆመ በማዘጋጃ ቤት ተቆጣጣሪዎች በዩኒቨርስቲው ውስጥ የቄራ አገልግሎት መደረግ እንደሌለበት ተገልጾ የቄራ አገልግሎት በማዘጋጃ ቤት በመደ[illegible] አጋጥሞ ያቆመ መሆኑን፤ የዶሮ እርባታ በመኖ እጥረት ምክን[illegible]ማቆሙን እንዲሁም የብሎኬት ማምረት ስራ ያቆመ በሲሚንቶ ዋጋ መናር መሆ[illegible]

92. በተጨማሪም በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት መልስ ኢንተርፕራይዙ በነባሩ መዋቅር ላይ ትክክለኛ የኮስት አካውንታት ተግባር ኃላፊነት የተሰጠ ሰራተኛ ባለመኖሩ የተፈጠረ ክፍተት መሆኑን እና በአዲስ መዋቅር ላይ እንዳለ እና መዋቅሩ ሲጸድቅ ተግበራዊ እንደሚያደርጉ ገልጸዋል፡፡

93. በኦዲቱ የመውጫ ስብሰባ ወቅት እና በረቂቅ የኦዲት ሪፖርት ምላሽ ላይ በሰጡት መልስ ኢንተርፕራይዙ የገቢ ማመንጫን ሲጀምረም ሆነ ሲዘጋ ለቦርድ የማያቀርበ በአዲስ ደንብ መሰረት ለቦርድ ተጠሪ ሆኖ ባለመቋቋሙ መሆኑን እና በነባሩ መዋቅር ላይ ባለው ክፍተት መሆኑን በመግለጽ ግኝቱን ተቀብለው ለወደፊት አዳዲስ ስራዎችን ሲከፈቱም ሆነ ሲዘጉ ጉዳዩን ለሚመለከታቸ ኃላፊዎች በማቅረብ እየተወሰኑ እንደሚተገበሩ ገልጸዋል፡፡

94. ኢንተርፕራይዙ አዳዲስ ለሚጀምራቸው የገቢ ማመንጫ ዘርፎች የአዋጭነት ጥናት ካላደረገ እና የዋጋ ተመን በቦርድ ካላጸደቀ፤ በተጨማሪም የገቢ ማመንጫዎችን ሲዘጋ ለቦርድ ካላሳወቀ የገቢ ማመንጫ ዘርፎች እንዳይበራከቱ እና አዋጭነታቸ እንዳይረጋገጥ እንዲሁም ትርፋማነታቸው እንዳይጨምር ከማድረጉም በላይ ኢንተርፕራይዙን ለኪሳራ ሊዳርግ ይችላል፡፡

ኢንተርፕራይዙ አገልግሎቶቹን እና ምርቶቹን የሚያስተዋቅበት ስርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ፡-

95. የገቢ ማመንጫ ኢንተርፕራይዙ አገልግሎቶቹን እና ምርቶቹን የሚያስተዋውቅበትን ስልቶች በመንደፍ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ በተጨማሪም ምርቶቹን ለተጠቃሚዎች የሚያሳይበት የመሸጫ ማዕከል (show room Display) ሊኖረ ይገባል፡፡

96. ይሁን እንጂ ኢንተርፕራይዙ ከ2012 ዓ.ም ጀምሮ አገልግሎቶቹን እና ምርቶችን የሚያስተዋቅበት ስልት በመንደፍ ተግባራዊ ያላደረገ መሆኑን፤ ምርቶቹን ለደንበኞቹ የሚያሳይበት የመሸጫ ማዕከላት (show room Display) በማቋቋም ተግባራዊ እንዳላደረገ እንዲሁም ይህንኑ ስራ የሚሰራ የገበያ ጥናትና ፕሮሞሽን ባለሙያ እንደሌለ ከተከለሰ ሰነዶች እና ለኢንተርፕራይዙ ማዕከላት በቀረበ ቃለ-መጠይቆች ለማወቅ ተችሏል፡፡

97. ስለጉዳዩ የኢንተርፕራይዙ የበላይ ኃላፊዎች በቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ፣ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ፣ በኦዲቱ የመውጫ ስብሰባ ወቅት እና ለረቂቅ ሪፖርት ላይ በሰጡት መልስ ኢንተርፕራይዙ አገልግሎትና ምርቶቹን ያስተዋወቀበት አሼ ሁኔታ ሸው

ፕሮግራምና ደቡብ ኤፍ ኤም 97.1 እና ኤፍ ኤም 100.9 ጋር የተሰራ ቢሆንም ነገር ግን በሚፈለገ ልክ አለመሆኑን/የተቋረጠ መሆኑን እንዲሁም የአገልግሎትና ምርት መሸጫ ማዕከል(show room Display) ያልተዘጋጀ መሆኑን እና ለወደፊት ለመስራት ያቀዱ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

98. ኢንተርፕራይዙ ምርትና አገልግሎቶቹን የሚያስተዋቅበት ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ባለማድረጉ የደንበኞቹን ቁጥር እንዳይጨምር እና የአቅርቦት አድማሱን እንዳያሰፋ እንዲሁም ኢንተርፕራይዙ ከሌሎች ድርጅቶች ጋር ተወዳደሪ እንዳይሆን እና የሚሰጣቸው ምርቶችና አገልግሎቶች እንዳይታወቁ አድርጎታል፡፡

የስራ አመራር ቦርዱ የኢንተርፕራይዙን አፈጻጸም ክትትል እና ግምገማ ማድረጉን በተመለከተ፤

99. የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲን በበላይነት የሚያስተዳድረ ቦርድ በከፍተኛ ትምህርት የገቢ ማስገኛ ድርጅቶች ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 456/2012 ዓ.ም አንቀፅ 7 ንኡስ አንቀፅ 1 መሰረት የኢንተርፕራይዙን አፈጻጸም ለመገምገም ቢያንስ በሶስት ወር አንድ ጊዜ ሊሰበሰብ እና ቃለ-ጉባኤ ሊይዝ ይገባል፡፡ በተጨማሪም ኢንተርፕራይዙን የሚከታተልና የሚደግፍ ኮሚቴ ሊያቋቁም ይገባል፡፡

100. ይሁን እንጂ ዩኒቨርሲቲውን በበላይነት የሚያስተዳድረ ቦርድ ከ2012 ዓ.ም ጀምሮ የኢንተርፕራይዙን አፈጻጸም ቢያንስ በሶስት ወር አንድ ጊዜ በመሰብሰብ ያልገመገመ መሆኑን እንዲሁም ኢንተርፕራይዙን የሚከታተል እና የሚደግፍ ኮሚቴ አቋቁሞ ተግባራዊ ያላደረገ መሆኑን በኦዲት ወቅት ከቀረበ ቃለ- መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

101. ስለጉዳዩ የኢንተርፕራይዙ የበላይ ኃላፊ በቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ ፣ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ፣ በኦዲት የመውጫ ስብሰባ ወቅት እና ለተላከላቸው ረቂቅ ሪፖርት ላይ በሰጡት መልስ ቦርዱ በየጊዜው እየተሰበሰበ የኢንተርፕራይዙን አፈጻጸም እንዳልገመገመ እና በስራ ላይ አለመሆኑን እና ይህ ክፍተት የመጣ የኢንተርፕራይዙ አዲስ መዋቅር ባለመጽደቁ መሆኑን እና መዋቅሩ ሲጸድቅ ተግባራዊ እንደሚደረግ ገልጸዋል፡፡

102. ቦርዱ በሶስት ወር አንድ ጊዜ ባለመሰብሰቡ በኢንተርፕራይዙ የሚያጋጥሙ የአሰራር ክፍተቶች እንዳይስተካከሉ እና በተሰሩ ስራዎች ላይ ግብረ-መልስ እንዳይሰጥ አድርጎታል፡፡

ኢንተርፕራይዙ የግምገማ ስርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ

103. የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ የገቢ ማመንጫ ኢንተርፕራይዝ ሥራ አፈጻጸሙን ቢያንስ በወር አንዴ ሊገመግም ይገባል፡፡

104. ይሁን እንጂ ኢንተርፕራይዙ ከ2012 በጀት ዓመት ጀምሮ በስሩ ያሉ ማዕከላት የስራ አፈጻጸማቸውን ወጥ በሆነ መልኩ በወር አንድ ግዜ ግምገማ የማያደርግ መሆኑን ለኢንተርፕራይዙ ማዕከላት በቀረበ ቃለ-መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

105. ስለጉዳዩ የኢንተርፕራይዙ የበላይ ኃላፊዎች በቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ በኢንተርፕራይዝ ደረጃ በየሩብ ዓመቱ ግምገማ እንደሚደረግ እና በፊት በየወሩ በኦፕሬሽን ዘርፍ ምክትል ስራ አስኪያጅ በኩል ይደረግ እንደነበር አሁን ላይ በየወሩ ግምግማ የማይደረግ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

106. በተጨማሪም በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት መልስ ኢንተርፕራይዙ ስራዎችን በማዕከላት ደረጃ በየሳምንቱ፣ በዘርፍ ደረጃ በየወሩ እና በኢንተርፕራይዝ ደረጃ በየሶስት ወሩ እንደሚገመግሙ ገልጸዋል፡፡

107. በኦዲት የመውጫ ስብሳባ እና ለተላከላቸው የረቂቅ ሪፖርት ላይ በሰጡት መልስ ኢንተርፕራይዙ አልፎ አልፎ ግምገማ እንደሚያደርግ ነገር ግን ቋሚ አለመሆኑን እና ግኝቱ ተቀብለው ወደፊት እንደሚያስተካክሉ በመግለጽ ክፍተቶቹ እንዳሉ ሆነ ኢንተርፕራይዙ የሂደባቸውን ሁኔታ የሚያሳይ ማስረጃ ማቅረባቸን ገልጸዋል፡፡

108. የኢንተርፕራይዙ የበላይ ኃላፊ ይህን ቢሉም ኢንተርፕራይዙ በማዕከላት፣ በዘርፍ እና በኢንተርፕራይዝ ደረጃ አፈጻጸሙን ስለመገምገሙ የሚያሳይ ማስረጃ/ቃለ-ጉባኤ ባለመቅረቡ እንዲሁም የቀረበ ማስረጃ በ2009 ዓ.ም የተደረገ የግምገማ ቃለ-ጉባኤ ሲሆን ከኦዲት ወሰን/scope ውጭ በመሆኑ የተሰጠውን ምላሽ አልተቀበልነም፡፡

109. ኢንተርፕራይዙ ወጥ የሆነ የግምገማ ስርዓት ካልዘረጋ በማዕከላት የሚሰሩ ስራዎች የአፈጻጸም ሂደት ምን ደረጃ ላይ እንደደረሰ እንዳይታወቅ እና በአሰራር ላይ የሚያጋጥሙ ችግሮች በወቅቱ እንዳይፈቱ ያደርጋል፡፡

የኢንተርፕራይዙ የመረጃ አያያዝና ልውውጥ ስርዓትን በተመለከተ

110. የገቢ ማመንጫ ኢንተርፕራይዙ አጠቃላይ የመረጃ አያያዝ ስርዓት በዘመናዊ ኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ (ICT) የተደገፈ ሊሆን ይገባል፡፡

111. ይሁን እንጂ የኢንተርፕራይዙ የመረጃ አያያዝ እና ልውውጥ ስርዓት በዘመናዊ ኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ስርዓት ያልተደገፈ መሆኑን እና ይህንኑ ስለሚሰራ ከፍተኛ የ ICT ባለሙያ በመዋቅሩ ላይ ቢፈቀድም ያልተሟላ መሆኑን ለኢንተርፕራይዙ

ዋና ጽ/ቤት እና በስሩ ላሉ ማዕከላት በቀረቡ ማስረጃዎች እና ቃለ-መጠይቆች ለማወቅ ተችሏል፡፡

112. የኢንተርፕራይዙ የበላይ ኃላፊ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ፣ በኦዲት የመውጫ ስብሰባ ወቅት እና በረቂቅ ሪፖርት ላይ በሰጡት መልስ ግኝቱን እንደተቀበሉት እና የኢንተርፕራይዙ አዲሱ መዋቅር መጽደቅን ተከትሎ የሚኖሩ ስራዎችንና ክፍሎችን መነሻ ተደርጎ የአውቶሜሽን ስራና መሰረተ ልማት ተመቻችቶ የሚተገበር መሆኑን ገልጸዋል፡፡

113. የኢንተርፕራይዙ የመረጃ ልውውጥ ስርዓት በዘመናዊ ኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን የተደገፈ አለመሆኑ መረጃዎች በቀላሉ እንዳይገኙ እንዲሁም ቀልጣፋ የሆነ አሰራር እንዳይሰፍን አድርጓል፡፡

ኢንተርፕራይዙ የሚጠቀምባቸው ማሽኖች ሲበላሹ አፋጣኝ ጥገና ማድረጉን በተመለከተ፤

114. የገቢ ማመንጫ ኢንተርፕራይዙ በስሩ ያሉ የስራ ክፍሎች (business units) የሚጠቀሙት መሳሪያዎች ወይም ማሽነሪዎች በሚበላሹበት ጊዜ አስቸኳይ ጥገና እንዲደረግላቸው ምቹ ሁኔታዎችን ሊያመቻች ይገባል፡፡

115. ይሁን እንጂ፡-

- በኢንተርፕራይዙ ማዕከላት የሚገኙ ማሽኖች ሲበላሹ አስቸኳይ ጥገና የማይደረግ መሆኑን፤
- በእርሻ ማዕከል በቂ የጥገና ባለሙያ አለመኖሩን እና በወተት ማቀነባበሪያ ማሽኖች ላይ ተደጋጋሚ ብልሽት ሲገጥም ከውጭ ባለሙያ መጥቶ ጥገና እንደሚደረግ እና ለማሽኑ ተብሎ የኤሌክትሪሻን ባለሙያ በመደቡ ላይ ቢፈቀድም ባለሙያ ያልተቀጠረ መሆኑን እንዲሁም በማዕከሉ ሶስት ትራክተሮች ያሉ ሲሆን ሁለቱ የማይሰሩ መሆኑን፤ በተጨማሪም ሶስት ጀኔሬተሮች ቢኖሩም ሁለቱ ጥገና የሚያስፈልጋቸው እና የማይሰሩ መሆኑን፤ እንዲሁም የመኖ ማቀነባበሪያ ማሽን ተጠግኖ ወደ ስራ እንዲገባ ያልተደረገ መሆኑን፤
- በሆቴል ማዕከሉ የመብራትና የውሃ መስመር መስተካከል አለመቻል፣ የሆቴሉ የህንፃ ሁኔታ አጠቃላይና መሠረታዊ ጥገና የሚያስፈልገው መሆኑን፣ የሕንፃውም የቀለም እድሳት ጉድለት ጨምሮ ያልተፈቱ ችግሮች መሆናቸው፤
- በወንዶ ገነት ደንና ተፈጥሮ ሀብት ኮሌጅ ዕደ-ጥበብ ማዕከል ሶስት የእንጨት መላጊያ ማሽኖች የማይሰሩ መሆኑ እንዲሁም በስራ ላይ ያሉት ማሽኖች

የአገልግሎት ዘመናቸው የቆየ በመሆኑ ጥገና ያልተደረገላቸ መሆኑ፤

- የግብርና ኮሌጅ ዕደ -ጥበብ ማዕከል የሽያጭ መመዝገቢያ ማሽን ተገዝቶ በዋና ጽ/ቤቱ ያለ ስራ የተቀመጠ መሆኑ እና ማዕከሉ ከ2012 ዓ.ም ጀምሮ ሽያጭ ሲያከናውን በሽያጭ መመዝገቢያ ማሽን አለመሆኑን ለማዕከሉ በቀረበ ቃለ-መጠይቅ ለማወቅ የተቻለ መሆኑ፤

ለኢንተርፕራይዙ ማዕከላት በቀረበ ቃለ-መጠይቅ እና ከተከለሱ ሰነዶች ለማወቅ ተችሏል፡፡

116. ስለጉዳዩ የኢንተርፕራይዙ የበላይ ኃላፊ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ፣ በኦዲት የመውጫ ስብሰባ ወቅት እና በረቂቅ ሪፖርት ላይ በሰጡት መልስ የተሰጠውን ግኝት እንደተቀበሉት እና የሚያስተካክሉ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

117. ኢንተርፕራይዙ በማዕከላት ላይ ያሉ ማሽነሪዎች ሲበላሹ አፋጣኝ ጥገና ወይም ቅያሪ ካልተደረገ ኢንተርፕራይዙ ምርቱን በቀላሉ እና በሚፈለግበት ሰዓት እንዳያመርት እንዲሁም ለገበያ እንዳያቀርብ እና ትርፋማ እንዳይሆን ያደርገዋል፡፡

ኢንተርፕራይዙ ተገቢን መረጃ ለሚመለከተው አካል ማሳወቁን በተመለከተ፤

118. የገቢ ማመንጫ ኢንተርፕራይዙ ተገቢን መረጃ/ የስራ አፈጻጸሙን በየሩብ አመቱ ለቦርድ እና ለትምህርት ሚኒስቴር ሊያቀርብ ይገባል፡፡

119. ይሁን እንጂ ኢንተርፕራይዙ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የገቢ ማስገኛ ድርጅቶች የሚተዳደሩበትን ሥርዓት ለመወሰን በወጣው መመሪያ ቁጥር 04/2012 ዓ.ም አንቀጽ 10 መሰረት ተገቢን መረጃ/ የስራ አፈጻጸሙን በየሩብ ዓመቱ (ከ2012-2014) ዓ.ም ለዩኒቨርሲቲው የሥራ አመራር ቦርድ እና ለትምህርት ሚኒስቴር ያላቀረበ መሆኑ በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

120. የኢንተርፕራይዙ የበላይ ኃላፊ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ፣ በመውጫ ስብሰባ ወቅት እና በረቂቅ ሪፖርት ምላሽ ላይ በሰጡት መልስ ግኝቱን እንደተቀበሉት እና አዲሱ መዋቅር ሲጸድቅ ተግባራዊ እንደሚደረግ ገልጸዋል፡፡

121. ኢንተርፕራይዙ ስለአፈጻጸሙ ተገቢውን መረጃ ለቦርድ እና ለትምህርት ሚኒስቴር ካላሳወቀ ድርጅቱ ያለበት ደረጃ እንዲሁም የተቋቋመበትን አላማ እየተወጣ መሆኑን እንዳይታወቅ ያደርጋል፡፡

የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ከሚሰጠው አገልግሎት ጋር ተያያዥ የሆኑ ገቢ ሊያስገኙ የሚችሉ አገልግሎቶች በዩኒቨርሲቲው የገቢ ማመንጫ ኢንተርፕራይዝ ሥር መደራጀታቸውን በተመለከተ፡-

122. የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ከሚሰጠው አገልግሎት ጋር ተያያዥ የሆኑ ገቢ ሊያስገኙ የሚችሉ አገልግሎቶች በዩኒቨርሲቲ ኢንተርፕራይዝ ሥር ሊደራጁ ይገባል፡፡

123. ይሁን እንጂ በሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ የገቢ ማመንጫ ኢንተርፕራይዝ ሲቋቋም በዩኒቨርሲቲው ሥር ካሉት የገቢ ማመንጫ ዘርፎች እና አገልግሎቶች ወደ ገቢ ማመንጫ ኢንተርፕራይዙ ተጠቃለው እንዲገቡ ለማድረግ በጽሁፍ የተደገፈ እና ምንን መነሻ እንዳደረገ የሚያሳይ መስፈርት ያልወጣ መሆኑን በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

124. ለዩኒቨርስቲው ለውስጥ ገቢ ማመንጫ ሪሶርስ ሞባላይዜሽን ዳይሬክቶሬት በቀረበ ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ በውስጥ ገቢ ስር ያሉት አገልግሎቶች ለዩኒቨርስቲ ሰራተኞች እና ተማሪዎች በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲያገኙ ሲባል መሆኑን እንዲሁም በውስጥ ገቢ ስር የተካተቱ አገልግሎቶች እና ምርቶች ከመማር ማስተማር ጋር ግንኙነት ያላቸው መሆኑን እና ወደ ኢንተርፕራይዙ የተካተቱ አገልግሎቶች አትራፊ የሆኑት መሆናቸውን ነገር ግን በጽሁፍ ደረጃ መስፈርት እንደሌለ ገልጸዋል፡፡

125. ስለጉዳዩ የኢንተርፕራይዙ የበላይ ኃላፊ በቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ ላይ በሰጡት መልስ ኢንተርፕራይዙ ሲቋቋም ከዩኒቨርስቲ ወደ ድርጅቱ የተላለፉ የገቢ ማመንጫ ዘርፎች በመስፈርት አለመሆኑን በተጨማሪም የኢንተርፕራይዙ የበላይ ኃላፊ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት ምላሽ የዩኒቨርሲቲው አመራር በወቅቱ ወደ ኢንተርፕራይዙ መግባት ያለባቸውን ዘርፎች ለይቶ የሰጣቸው መሆኑን ገልጸዋል፡፡

126. በተጨማሪም በኦዲቱ የመውጫ ስብሰባ ወቅት የዩኒቨርሲቲው የበላይ ኃላፊ በሰጡት መልስ ከዩኒቨርስቲው ወደ ኢንተርፕራይዙ እንዲተላለፉ የተደረጉ የገቢ ማመንጫ ዘርፎች ትርፋማነትን መሰረት በማድረግ እና ወደ ኢንተርፕራይዙ ቢገቡ የበለጠ ትርፍ ያስገኛሉ ተብሎ የታመነባቸውን መሆኑን ነገር ግን በሰነድ ደረጃ የተጻፈ ነገር አለመኖሩን ገልጸዋል፡፡

127. የኢንተርፕራይዙ የበላይ ኃላፊ ይህን ቢሉም የገቢ ማስገኛ ዘርፎች ከዩኒቨርስቲ ወደ ኢንተርፕራይዙ ሲተላለፉ ምንን መነሻ አድርገው እንደሆነ ግልጽ የሆነ መስፈርት ባለመውጣቱ የተሰጠውን ምላሽ አልተቀበልነውም፡፡

128. ዩኒቨርስቲ ወደ ኢንተርፕራይዙ የተላለፉ የንግድ እና የአገልግሎት ዘርፎች መስፈርት አውጥቶ በመስፈርቱ መሰረት ተግባራዊ አለመደረጉ የገቢ ማመንጫ ዘርፎች ተፈላገውን

ያህል ውጤት እንዳያመጡ እንዲሁም ከፍተኛ ገቢ ወይም ትርፍ የሚያስገኙ የንግድ ዘርፎች እና አገልግሎቶች ወደ ኢንተርፕራይዙ እንዳይጠቃለሉ አድርጓል፡፡

ክፍል ሦስት

መደምደሚያ

129. የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ የገቢ ማመንጫ ኢንተርፕራይዝ እና የውስጥ ገቢ ማመንጫ(ሪሶርስ ሞባላይዜሽን) የስራ አፈፃፀም ውጤታማነትን በተመለከተ የሚከተሉት ግድፈቶችና ጉድለቶች ተገኝተዋል፡፡

- የሀዋሳ ዩኒቨርስቲ የገቢ ማመንጫ ኢንተርፕራይዝ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 456/2012 ዓ.ም መሰረት በዩኒቨርስቲ ሥራ አመራር ቦርድ እየተመራ አይደለም፡፡ ኢንተርፕራይዙ የስራ ዕቅዱን፣ ፕሮግራሙን፣ በጀቱን፣ የግዥ ዕቅዱ አዘጋጅቶ ለቦርድ በማቅረብ እና በማጸደቅ ተግባራዊ አላደረገም፣ ዕቅድ አፈጻጸሙም ቀርቦ አልተገመገመም፡፡
- የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ የገቢ ማመንጫ ኢንተርፕራይዝ ሲቋቋም ከዩኒቨርሲቲው በአይነት የተሰጠ ሀብት ግምቱ በባለሙያ ተገምቶ የኢንተርፕራይዝ ካፒታል ውስጥ አልተካተተም፡፡ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 456/2012 መሰረት የኢንተርፕራይዙ ካፒታል ድጋሚ በባለሙያ ተገምቶና በቦርድ ተወስኖ አልተሻሻለም፡፡
- ኢንተርፕራይዙ ከሚያገኘው የተጣራ ትርፍ ላይ 80 በመቶን ለዩኒቨርስቲው ተልዕኮና አላማ ማስፈጸሚያ መዋል ሲገባው እንዲውል አልተደረገም፡፡
- ኢንተርፕራይዙ ከ2012 ዓ.ም ጀምሮ ሂሳቡን በዋና ኦዲተር ወይም እርሱ በሰየመው አካል ኦዲት አላስደረገም፡፡
- ኢንተርፕራይዙ በሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ያሉ ባለሙያዎችን በጊዜያዊነት እንዴት እንደሚጠቀምባቸው ግልጽ የሆነ መስፈርት አላወጣም፡፡ ህጋዊ ሰውነትና የንግድ ፈቃድ ለሌላቸው ማህበራት ውል እያስገባ ስራ እያሠራ መሆኑ፣ በተጨማሪም ኢንተርፕራይዙ የዩኒቨርሲቲ ባለሞያዎችን ሲጠቀም ኮንትራት አሰጣጥ እና ክፍያ አተማመን ህጋዊ የአሰራር ስርዓት አልዘረጋም፡፡
- ኢንተርፕራይዙ በአገልግሎት አሰጣጡ ዙሪያ የሚቀርቡ ቅሬታዎች የሚስተናግዱበትን ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ አላደረገም፡፡
- የገቢ ማመንጫ ኢንተርፕራይዙ ለሚያቀርባቸው ምርቶች/ አገልግሎቶች ክፍያዎችን በውሉ መሰረት እና በወቅቱ የማይሰበስብ መሆኑ፤ ለሐዋሳ ዩኒቨርሲቲ የአዲስ አበባ እንግዳ ቤት ግዥ ከኢንተርፕራይዙ በ2009 ወጪ

የተደረገ ገንዘብ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ እንዲመለስ አልተደረገም፡፡

- ኢንተርፕራይዙ አፈጻጸሙን የውስጥ ኦዲት በማድረግ የኦዲት ሪፖርት እንዲቀረብ አልተደረገም፡፡
- ኢንተርፕራይዙ የገቢ ማመንጫ ዘርፎችን ያላስፋፋ መሆኑ እንዲሁም የድርጅቱን ትርፋማነት እንዲጨምር የማጠናከር ስራ አልተሰራም፡፡
- ኢንተርፕራይዙ በስሩ ባሉት የስራ ክፍሎች (business units) ለሚገኙ ሰራተኞች የአቅም ክፍተት በመለየት፣ አስፈላጊውን የሙያ እና ክህሎት ስልጠና በዕቅዱ መሰረት እንዲሰጥ አልተደረገም፡፡
- ኢንተርፕራይዙ የንግድ ዘርፎችን ሲጀምርም ሆነ ሲዘጋ ለቦርድ አያሳውቅም፡፡
- ኢንተርፕራይዙ አገልግሎቶቹን/ ምርቶችን የሚያስተዋውቅበትን ስልት እንዲሁም ምርቶችን የሚያሳይበት የመሸጫ ማዕከል (show room Display) አላቋቋመም፡፡
- የኢንተርፕራይዙ የመረጃ አያያዝ እና ልውውጥ ስርዓት በዘመናዊ ኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ (ICT) የተደገፈ አይደለም፡፡
- ኢንተርፕራይዙ በስሩ ያሉ የስራ ክፍሎች (business units) የሚጠቀሙት መሳሪያዎች ወይም ማሽነሪዎች በሚበላሹበት ጊዜ አስቸኳይ ጥገና አይደረግም፡፡
- የገቢ ማመንጫ ኢንተርፕራይዙ የስራ ማዕከላትን የስራ አፈጻጸም እየገመገመ አይደለም፡፡
- ኢንተርፕራይዙ አጠቃላይ አፈጻጸሙን በተመለከተ ተገቢን መረጃ በየሩብ አመቱ ለቦርድ እና ለትምህርት ሚኒስቴር እንዲቀርብ ኣላደረገም፡፡
- በሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ወደ ገቢ ማመንጫ ኢንተርፕራይዙ የተካተቱ አገልግሎቶችና ምርቶች በመስፈርት አለመሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡

ስለሆነም በኦዲቱ ወቅት የተገኙትን ድክመቶች እና ችግሮች ለማስወገድ ወይንም ለማቃለል አስተዋጽኦ ያደርጋሉ ብለን ያመንባቸውን የማሻሻያ ሃሳቦች በሚቀጥለው የሪፖርቱ ክፍል አቅርበናል፡፡

ክፍል አራት

የማሻሻያ ሃሳቦች

130. የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ የገቢ ማመንጫ ኢንተርፕራይዝ እና የውስጥ ገቢ ማመንጫ(ሪሶርስ ሞባላይዜሽን) አፈጻጸም ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መልኩ የሚከናወንበትን ሥርዓት ተግባራዊ ለማድረግ ያስችላሉ ያልናቸውን የሚከተሉትን የማሻሻያ ሃሳቦች አቅርበናል፡፡

- የሀዋሳ ዩኒቨርስቲ የሥራ አመራር ቦርድ የገቢ ማመንጫ ኢንተርፕራይዙ የረጅም የመካከለኛ እና አመታዊ የስራ ዕቅዱን ለእሱ ማስፈጸሚያ የሚያፈልገን በጀት ማዘጋጀቱን እና ከዩኒቨርሲቲ ተልዕኮ ጋር የተጣጣመ መሆኑን ቢያንስ በየሶስት ወሩ በመገምገም ሊያጸድቅ እና አፈጻጸሙንም በየጊዜ መገምገም አለበት፡፡ ኢንተርፕራይዙ ለአመቱ ሥራ የሚያስፈልገን የግዥ ዕቅድ ፍላጎት በማዘጋጀትና ለሥራ አመራር ቦርድ በማቅረብ እና በማጸደቅ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ በተጨማሪም የሚቀርቡ ቅሬታዎች የሚስተናገዱበት የአሰራር ሥርዓት መዘርጋቱንና መተግበሩን ቦርዱ ማረጋገጥ ይጠበቅበታል፡፡
- የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ የገቢ ማመንጫ ኢንተርፕራይዝ ሲቋቋም ከዩኒቨርሲቲ በአይነት የተሰጠ ሀብት ግምቱ በባለሙያ ተገምቶ እና በኦዲተር ተረጋግጦ የኢንተርፕራይዝ ካፒታል ውስጥ መካተት ያለባቸው ሲሆን ተግባራዊነቱንም የሥራ አመራር ቦርዱ ሊከታተል ይገባል፡፡
- ኢንተርፕራይዙ በየአመቱ በIFRS መሰረት የሂሳብ መግለጫዎቹን በማዘጋጀት ኦዲት ያልተደረጉትን አመታት የሂሳብ መግለጫዎችን ጭምር በፌዴራል ዋና ኦዲተር ወይም እርሱ በሚሰይመው የኦዲት ተቋም ኦዲት ማስደረግ ይጠበቅበታል፡፡ በተቋሙ የሂሳብ መግለጫዎች ላይ የሚታዩ ተሰብሳቢ ገንዘቦችን ለዩኒቨርሲቲ የእንግዳ ማረፊያ የተሰጠን ብር 35,075,000 ጨምሮ ትኩረት ሰጥቶ ሊሰበስብ፣ የማይሰበሰቡ ሂሳቦችም ካሉ ምክንያታቸው ተጣርቶ በህግ መሰረት ከሂሳብ መዝገብ እንዲሰረዙ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡ በተጨማሪም ኢንተርፕራይዙ ከሚያገኘው የተጣራ ትርፍ ላይ 80 በመቶን ለዩኒቨርስቲው ተልዕኮና አላማ ማስፈጸሚያ በህጉ መሰረት ማዋል ይኖርበታል፡፡ የሥራ አመራር ቦርዱም ይህ መደረጉን እና በዩኒቨርሲቲ በጀት ውስጥ መካተቱን ማረጋገጥ ይጠበቅበታል፡፡
- ኢንተርፕራይዙ የንግድ ፈቃድ ያወጣባቸውን የማማከር፣ የጥናት እና ተዛማች ሥራዎች ለማሰራት የዩኒቨርሲቲን አካዳሚክ ባለሙያዎች ሲጠቀም በሥራ

ላይ ያሉ ህጎችን በማይቃረን መልኩ ግልጽ መስፈርት በማዘጋጀትና የአሰራር ሥርዓት በመዘርጋት በዩኒቨርሲቲ የሥራ አመራር ቦርድ በማጸደቅ ወደ ተግባር ሊገባ ይገባል፡፡ ህጋዊ ሰውነት ከሌላቸው ማህበራት ጋር የሚያደርጋቸውን ስምምነት ሊያቆም እና ህጋዊ ዕውቅና እና የንግድ ፈቃድ ካላቸው አካላት ጋር ብቻ ውል መግባት ይጠበቅበታል፡፡ በተጨማሪም በጊዜያዊነት ለሚቀጥራቸው ባለሙያዎች የሚከፈል ክፍያ፣ አበል ሆነ ሌላ ወጪዎች መስፈርትና ተመን በማዘጋጀት እና በቦርድ በማጸደቅ ወደ ሥራ ሊገባ እና በሥራ አመራር ቦርዱ ባልጸደቀ መስፈርትና ተመን የሚያደርጋቸውን ክፍያ ሊያቆም ይገባል፡፡ በረቂቅ ደረጃ ተዘጋጅተዋል የተባሉት ኢንተርፕራይዙ አደረጃጀት፣ መዋቅር እና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮችም በፍጥነት ለሥራ አመራር ቦርድ ቀርበ በማጸደቅ ወደ ተግባር ሊገቡ ይገባል፡፡ ያለቦርድ ውሳኔ የተከፈሉ ክፍያዎችን፣ የማበረታቻ (ቦነሶችና)፣ አበሎችን በውስጥ ኦዲት በማጣራት ክፍያዎቹ እንዲከፈሉ የፈቀዱ አካላት ተጠያቂ ሊያደርግ እና ተመላሽ መደረግ ያለበትም ከሆነ በማጣራት ተመላሽ ማስድረግ አለበት ቦርዱም ይህ መፈጸሙን ማረጋገጥ ይጠበቅበታል፡፡

- ኢንተርፕራይዙ የውስጥ ኦዲቱን በማጠናከር በየጊዜ የኢንተርፕራይዙን ሂሳብ እና ንብረት እንዲሁም ሌሎች ተግባራትን ኦዲት በማድረግ ለኢንተርፕራይዙ አመራር እና ለሥራ አመራር ቦርድ እንዲያቀርብና ክፍተቶች በአፋጣኝ እርምጃ የሚወሰዱበትን ሁኔታ ሊፈጥር ይገባል፡፡
- ኢንተርፕራይዙ በስሩ የሚገኙ ሰራተኞችን የአቅም ክፍተት ለይቶ እና አቅዶ በዕቅዱ መሰረት ስልጠና በመስጠት በድርጅቱ ያሉ ሰራተኞች ከአዳዲስ አሰራር ጋር እንዲላመዱ እንዲሁም እራሳቸውን እንዲያጎለብቱ በማድረግ የአሰራር ቅልጥፍና፣ ውጤታማ እና ምርታማ የሆነ አሰራር እንዲፈጠር ማደረግ ይኖርበታል፡፡
- ኢንተርፕራይዙ አዳዲስ ለሚከፍታቸው የንግድ ስራዎች የአዋጪነት ጥናት በማጥናት፣ የዋጋ አተማመን በቦርድ ሊያስወስን እንዲሁም የገቢ ማመንጫዎችን ሲጀምርም ሆነ ሲዘጋ ለቦርድ አሳውቆ ውሳኔ እንዲሰጥበት ሊያደርግና ህጋዊ የአሰራር ስርዓትን ሊከተል እና ተጠያቂነትን በማጠናከር ድርጅቱን ትርፋማ እና ውጤታማ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡
- ኢንተርፕራይዙ አገልግሎቶቹን እና ምርቶችን በማስተዋወቅ እንዲሁም የማሳያ እና የመሸጫ ማዕከል (show room Display) በተለያዩ ቦታዎች አቋቁሞ ድርጅቱ

ለደንበኞች ያለውን ተደራሽነት በማስፋት ትርፋማነቱ እና የገቢ መጠኑ
እንዲጨምር፣ ምርቶችን ለመሸጥ የሚንቀሳቀስበትን ወጪ እንዲቀንስ እና ከሌሎች
አቻ ድርጅቶች ጋር ተወዳደሪ እንዲሆን ማድረግ ይገባዋል፡፡

➢ ኢንተርፕራይዙ የመረጃ አደረጃጀት፣ አያያዝ እና ልውውጥ ስርዓቱን በማዘመን
አጠቃላይ የመረጃ አያያዝ ስርዓቱ በዘመናዊ ኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ
(ICT) የተደገፈ በማድረግ የመረጃ ለውውጥ ስርዓቱ ወጪ ቆጣቢ፣ ፈጣንና ቀልጣፋ
እንዲሁም ውጤታማ እንዲሆን ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡

➢ ኢንርፕራይዙ በስሩ ባሉ የስራ ማዕከላት የሚበላሹ ማሽኖችን በአፋጣኝ ጥገና እና
ቅያሬ በማድረግ እንዲሁም ዘመናዊ የማምረቻ መሳሪያዎችን በመጠቀም
በተቀላጠፈ መልኩ ስራዎችን በማጠናቀቅ ምርታማነቱን ማሻሻል ይኖርበታል፡፡

➢ ኢንተርፕራይዙ ስለ ስራ አፈጻጸሙ ተገቢውን መረጃ በህግ አግባብ መሰረት
ለትምህርት ሚኒስቴር እና ለቦርድ እያሳወቀ ድርጅቱ የተቋቋመበትን አለማ እያሳካ
መሆኑን ማረጋገጥ ይጠበቅበታል፡፡

➢ የሀዋሳ ዩኒቨርስቲን በበላይነት የሚያስተዳድረው ቦርድ በየሶስት ወር እየተሰበሰበ
የኢንተርፕራይዙን አፈጻጸም በመገምገም በኢንተርፕራይዙ የአሰራር ክፍተቶች
ካሉ መፍትሄ እንዲያገኙ እንዲሁም መጠናከር ያለባቸው ጉዳዮች እንዲጠናከሩ
እና የተቋቋመበትን አላማ እየተወጣ መሆኑን ሊከታተል እና ሊቆጣጠር ይገባዋል፡፡
በተጨማሪም ቦርዱ የኢንተርፕራይዙን የተለያዩ ስራዎችን በቅርበት የሚከታተል
እና የሚደግፍ ኮሚቴ በማቋቋም ማገዝ ይጠበቅበታል፡፡

➢ ኢንተርፕራይዙ ወጥ በሆነ መልኩ የሥራ አፈጻጸሙን ቢያንስ በወር አንዴ
እየገመገመ በማዕከላት የሚሰሩ ስራዎች በታቀደላቸው መሰረት እየሄዱ መሆኑን
ሊያረጋግጥ እና በሚያጋጥሙ ችግሮች ላይ አፋጣኝ ምላሽ/ግብረ መልስ እንዲያገኙ
ማድረግ ይኖርበታል፡፡

በመጨረሻም በኦዲቱ ወቅት የኢንተርፕርይዙ እና የዩኒቨርሲቲው የበላይ ኃላፊዎች፣
አመራሮችና ሰራተኞች፣ እንዲሁም በኦዲቱ ወቅት መረጃ የተሰበሰበባቸው
የኢንተርፕራይዙ ማዕከላት እና የዩኒቨርስቲው ኮሌጆች ላደረጉልን የሥራ ትብብር
እናመሰግናለን፡፡

አባሪ፡ 1 የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ገቢ ማመንጫ ኢንተርፕራይዝ ኃላ/የተ/የግ/ማህበር ድርጅታዊ መዋቅር



አባሪ 2 ፡- የመመዘኛ መስፈርት (Evaluative Criteria)

የኦዲት ተደራጊ መ/ቤት፡- <u>የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ</u>

የኦዲቱ አካባቢ፡- <u>የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ የገቢ ማመንጫ ኢንተርፕራይዝ እና የውስጥ ገቢ (ሪሶርስ ሞብላይዜሽን) የስራ አፈፃፀም ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ መሆኑን በተመለከተ</u>

የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issues)	የመመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative Criteria)
1. የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ የገቢ ማመንጫ አስተዳደር እና አሰራር የሀገሪቱን ህግና ስርዓትን የተከተለ፣ ቀልጣፋ እና ጤታማ መሆኑን መገምገም፤	1) የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ የገቢ ማስገኛ ተቋም በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 456/2012 መሰረት ለዩኒቨርሲቲ ቦርድ ተጠሪ ሊሆን ይገባል፡፡ (ምንጭ፡ ደንብ ቁጥር 456/2012 አንቀፅ 5 ንኡስ አንቀፅ 1 እና አንቀፅ 6 ንኡስ አንቀፅ 1)
	2) የሐዋሳ ዩኒቨርሲቲ ከሚሰጠው አገልግሎት ጋር ተያያዥ የሆኑ የገቢ ሊያስገኙ የሚችሉ አገልግሎቶች በዩኒቨርሲቲ ኢንተርፕራይዝ ሥር ሊደራጁ ይገባል፡፡ (ምንጭ፡ ደንብ ቁጥር 456/2012 አንቀፅ 2 ንኡስ አንቀፅ 2፣ የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የገቢ ማስገኛ ድርጅቶች የሚተዳደሩበትን ሥርዓት ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 04/2012 አንቀጽ 5)
	3) የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ የገቢ ማስገኛ ድርጅት ካፒታል በባለሞያዎች በትክክል ተገምቶና በኦዲተር ተረጋግጦ ሊቋቋም ይገባል፡፡ (ምንጭ፡ የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የገቢ ማስገኛ ድርጅቶች የሚተዳደሩበትን ሥርዓት ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 04/2012 አንቀጽ 7/3)
	4) የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ኢንተርፕራይዝ የተፈቀደ ካፒታል በዩኒቨርሲቲው የሥራ አመራር ቦርድ ሊወሰን እና ከተወሰነበት ጊዜ አንስቶ በአምስት አመት ውስጥ ተከፍሎ ሊጠናቀቅ ይገባል፡፡ (ምንጭ፡በደንብ ቁጥር 456/2012፣ የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የገቢ ማስገኛ ድርጅቶች የሚተዳደሩበትን ሥርዓት ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 04/2012 አንቀጽ 7/1-2
	5) ኢንተርፕራይዙ በንግድ ህጉ መሰረት ሊመዘገብና ፈቃድ ሊያወጣ ይገባል፡፡ (ምንጭ፡-የንግድ ምዝገባ አዋጅ ቁጥር 980/2008 አንቀፅ 6 ንኡስ አንቀፅ 3)
	6) ኢንተርፕራይዙ በየአመቱ አይ.ኤፍ አር.ኤስ መሰረት ሂሳቡን ሊዘጋ እና ኦዲት ሊደረግ ይገባል፡፡ ምንጭ፡ ደንብ ቁጥር 456/2012 አንቀጽ 12/3 የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የገቢ ማስገኛ ድርጅቶች የሚተዳደሩበትን ሥርዓት ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 04/2012 አንቀጽ 9/
	7) ኢንተርፕራይዙ በሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ያሉ ባለሙያዎችን በገበያዊነት እንዴት እንደሚጠቀምባቸው ግልጽ የሆነ መስፈርት ሊያወጣና በሚመለከተው አካል በማጸደቅ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ (ምንጭ፡ የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የገቢ ማስገኛ ድርጅቶች

የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issues)	የመመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative Criteria)
	የሚተዳደሩበትን ሥርዓት ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 04/2012)
	8) ኢንተርፕራይዙ የዩኒቨርሲቲ ባለሞያዎችን ሲጠቀም ኮንትራት አሰጣጥ እና ክፍያ አተማመን ህጋዊ የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋና በሚመለከተው አካል በማጸደቅ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ (ምንጭ፡ መልካም ተሞክሮ)
	9) የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ የገቢ ማስገኛ ድርጅት በየዓመቱ የሚያገኘውን ከተጣራ ትርፍ ካፒታሉ ተከፍሎ እስኪያልቅ 40% እና ተከፍሎ ሲያልቅ 80% ለዩኒቨርሲቲው ተልዕኮና ዓላማ ማስፈፀሚያ ሊያውል ይገባል፡፡ (ምንጭ፡ የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የገቢ ማስገኛ ድርጅቶች የሚተዳደሩበትን ሥርዓት ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 04/2012)
	10) የገቢ ማስገኛ ድርጅቱ የሚተዳደርበትን የውስጥ የአሰራር ዝርዝር መመሪያ ሊያዘጋጅ እና በሚመለከተ አካል በማጸደቅ ተግባራዊ ሊያርግ ይገባል፡፡ (ምንጭ፡ የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የገቢ ማስገኛ ድርጅቶች የሚተዳደሩበትን ሥርዓት ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 04/2014 እና ደንብ ቁጥር 456/2012 አንቀፅ 8 ንኡስ አንቀፅ 3)
	11) የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ የገቢ ማስገኛ ኢንተርፕራይዝ አደረጃጀት፣ የደመወዝና ጥቅማ ጥቅም በማዘጋጀትና በዩኒቨርሲቲ የሥራ አመራሩ በማጸደቅ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ (ምንጭ፡- የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 456/2012 ሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ገቢ ማመንጫ ኢንተርፕራይዝ የ2013 በጀት ዓመት የእቅድ አፈጻጸም ሪፖርት)
	12) የገቢ ማስገኛ ድርጅቱን የአገልግሎት አሰጣጥ በሚመለከት የሚቀርቡ ቅሬታዎች የሚስተናገዱበት ስርዓት ተዘርግቶ ተግራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ (ምንጭ፡ ደንብ ቁጥር 456/2012 አንቀፅ 6 ንኡስ አንቀፅ 3)
	13) የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ የገቢ ማስገኛ ኢንተርፕራይዝ የስራ ፕሮግራምና በጀት አዘጋጅቶ ለቦርድ ሊያቀርብ እና ሲፀድቅም ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ (ምንጭ፡ ደንብ ቁጥር 456/2012 አንቀፅ 8 ንኡስ አንቀፅ 4)
	14) የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ በኢንተርፕራይዙ ሥር ያልተካተቱ በገቢ ማመንጫ ክፍሎቹ አማካኝነት ያገኘን ገቢ በፋይናንስ ህጉ መሰረት ሥራ ላይ ሊያውል ይገባል፡፡ (ምንጭ፡-የሚኒስትሮች ም/ቤት ደንብ ቁ. 190/2002 አንቀጽ 28 ንዑስ አንቀጽ 2፣ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የውስጥ ገቢ መመሪያ ቁጥር 39/2006 አንቀጽ 2፣ 3 እና 4)
	15) ለገቢ ማመንጫ የወጣ ወጪ እና የተገኘ ገቢ በሚመለከት የሂሳብ መግለጫ ላይ ሊታይ ይገባል፡፡ (ምንጭ፡ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የውስጥ ገቢ መመሪያ ቁጥር 39/2006 አንቀጽ 8)
	16) ዩኒቨርሲቲው ለሚሰጠው የገቢ ማስገኛ የሚያስከፍለው ዋጋ ተመን ሥልጣን በተሰጠ አካል ሊጸደቅ ይገባል፡፡ (ምንጭ፡- በፋይናንስ አስተዳደር የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር

የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issues)	የመመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative Criteria)
	190/2002 አንቀጽ 21 ንዑስ አንቀጽ 1)
የገቢ ማመንጫ ኢንተርፕራይዙ የገቢ ማመንጫ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የተዘረጋ ሥርዓት ኢኮኖሚያዊ ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መልኩ ማሳደጉን መገምገም፣	17) የገቢ ማመንጫ ኢንተርፕራይዙ በስሩ ላሉት የስራ ክፍሎች (business units) ግዥ ለመፈጸም የሚረዳ የግዥ መመሪያ በማዘጋጀት በቦርዱ ሊያጸድቅና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ (ምንጭ፡- ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርቶች እና የቅኝት ኦዲት ቃለ-መጠይቅ)
	18) የገቢ ማመንጫ ኢንተርፕራይዙ የግዥ ዕቅድ በማዘጋጀትና በሥራ አመራር ቦርዱ በማጸደቅ በዕቅዱ መሰረት ሊተገበር ይገባል፡፡ (ምንጭ፡ የመንግስት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁር /25/84 አንቀፅ 14 ንኡስ አንቀፅ 4)
	19) የገቢ ማመንጫ ኢንተርፕራይዙ ለሚያቀርባቸው ምርቶች/ አገልግሎቶች ክፍያዎችን በውል መሰረት ሊሰበሰብ ይገባል፡፡ (ምንጭ፡-የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ገቢ ማመንጫ ኢንተርፕራይዝ የ2012 በጀት ዓመት የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት)
	20) ኢንተርፕራይዙ የውስጥ ቁጥጥር እንዲሁም የውስጥ ኦዲት ስርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊያደረግ ይገባል፡፡ (ምንጭ፡-የፌዴራል መንግስት የውስጥ ቁጥጥር ደረጃዎች መመሪያ ቁጥር 8/2003)
	21) ኢንተርፕራይዙ የገቢ ማመንጫ ዘርፎችን በማጠናከር እና በማስፋፋት ትርፋማነቱን ሊያሳድግ ይገባል፡፡ (ምንጭ፡ መልካም ተሞክሮ)
	22) የገቢ ማመንጫ ኢንተርፕራይዙ በስሩ ባሉት የስራ ክፍሎች (business units) ለሚገኙ ሰራተኞች የአቅም ክፍተት በመለየት፣ አስፈላጊውን የሙያ እና ክህሎት ስልጠና ሊሰጥ ይገባል፡፡ (ምንጭ፡- መልካ ተሞክሮ)
የገቢ ማመንጫ ኢንተርፕራይዙ የሀብት አስተዳደር፣ የገቢያ ጥናት እና መረጃ አያያዝና ልውውጥ ስርዓት በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ መሆኑን መገምገም፣	23) የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ የገቢ ማመንጫ ኢንተርፕራይዝ አዳዲስ ለሚከፍታቸው የንግድ ስራዎች የአዋጪነት ጥናት ሊኖረ ይገባል፡፡ (ምንጭ፡-መልካም ተሞክሮ)
	24) ኢንተርፕራይዙ አዳዲስ የገቢ ማመንጫዎችን ሲጀምርም ሆነ ሲዘጋ ከቦርዱ ፈቃድ ሊያገኝ ይገባል፡፡ (ምንጭ፡ መልካም ተሞክሮ)
	25) የገቢ ማመንጫ ኢንተርፕራይዙ አገልግሎቶቹን (ምርቶችን) የማስተዋወቅ ስልቶችን በመንደፍ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ (ምንጭ፡- የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ገቢ ማመንጫ ኢንተርፕራይዝ የ2012 በጀት ዓመት የፋይናንሻል የኦፕሬሽን ዕቅድ እና የቅኝት ኦዲት ቃለ-መጠይቅ)

የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issues)	የመመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative Criteria)
	26) የገቢ ማመንጫ ኢንተርፕራይዙ ምርቶቹን ለተጠቃሚዎች የሚያስተዋወቅበት እና መሸጫ ማዕከል (show room Display) ሊኖረ ይገባል፡፡ (ምንጭ፡- መልካም ተሞክሮ)
	27) የገቢ ማመንጫ ኢንተርፕራይዙ በስሩ ባሉ የስራ ክፍሎች ስለሚገኙ ሰራተኞች አጠቃላይ መረጃና ፋይል በማዘጋጀት በአግባቡ አደራጅቶ ሊይዝ ይገባል፡፡ (ምንጭ፡-የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ገቢ ማመንጫ ኢንተርፕራይዝ የ2012 በጀት ዓመት የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት)
	28) የገቢ ማመንጫ ኢንተርፕራይዙ አጠቃላይ የመረጃ አያያዝ ስርዓት በዘመናዊ ኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ (ICT) የተደገፈ ሊሆን ይገባል፡፡ (ምንጭ፡- መልካም ተሞክሮ)
	29) የገቢ ማመንጫ ኢንተርፕራይዙ በስሩ ያሉ የስራ ክፍሎች (business units) የሚጠቀሙት መሳሪያዎች ወይም ማሽነሪዎች በሚበላሹበት ጊዜ አስቸኳይ ጥገና እንዲደረግላቸው ምቹ ሁኔታዎችን ሊያመቻች ይገባል፡፡ (ምንጭ፡- የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ገቢ ማመንጫ ኢንተርፕራይዝ የ2012 በጀት ዓመት የፋይናንሻል የኦፕሬሽን ዕቅድ)
	30) የገቢ ማመንጫ ኢንተርፕራይዙ ተገቢን መረጃ በየሩብ አመቱ ለቦርድ እና ለትምህርት ሚኒስቴር ሊያቀርብ ይገባል፡፡ (ምንጭ፡ የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የገቢ ማስገኛ ድርጅቶች የሚተዳደሩበትን ሥርዓት ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 04/2012)
	31) የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲን በበላይነት የሚያስተዳድር ቦርድ ቢያንስ በሶስት ወር አንድ ጊዜ ሊሰበሰብ እና ቃለ-ጉባኤ ሊይዝ ይገባል፡፡ (ምንጭ፡ ደንብ ቁጥር 456/2012 አንቀፅ 7 ንኡስ አንቀፅ 1)
	32) የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ የገቢ ማመንጫ ኢንተርፕራይዝ ሥራ አፈጻጸሙን ቢያንስ በወር አንዴ ሊገመግም ይገባል፡፡ (ምንጭ፡መልካም ተሞክሮ)

አባሪ፡- 3 በዩኒቨርስቲው የማማከር አገልግሎት ማህበር የተሰሩ ስራዎች

ተ.ቁ	የአሰሪ መስሪያ ቤት/ድርጅት ስም	የፕሮጀክቱ አይነት	የፕሮጀክቱ አጠቃላይ ዋጋ
1	በ2009 ዓ.ም ለደቡብ ክልል የውሃና መስኖ ልማት ቢሮ (በውሃና ወሃ ነክ ማህንዲሶች ማማከር ማህበር አማካኝነት)	የብላቴ ወንዝ የውሃ በጀት ጥናት	6,697,558.19
3	2010 ዓ.ም የቢልት ሀላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር (በሲቪል ማሃንዲሶች አጠቃላይ የዲዛይን፣ሱፐርቪዢን ማህበር አማከኝነት)	የG+4 ህንጻ የሆቴል አገልግሎት የዲዛይን ሪቪው ስራ	41,043.50
4	በ2009 ዓ.ም ለደቡብ ክልል የአርብቶ አደር ጉይዮች ቢሮ የማማከር ስራ (በውሃና ወሃ ነክ ማሀንዲሶች ማማከር ማህበር)	በደቡብ ኦሞ ዞን በማሌ ወረዳ ቤዞ-ቦኮ የመስኖ ግንባታ ጥናት ዲዛይን ማማከር (SNNPR pastoral Affaires bureau) study and re-design of bezo tiki-boko irrigation scheme at south omo zone male worda)	477,354.92
5	በ2010 ዓ.ም(NOV,2018) ለደቡብ ክልል የውሃና መስኖ ልማት ቢሮ (በውሃና ወሃ ነክ ማሀንዲሶች ማማከር ማህበር)	የirrigation potential assessment studies) የማማከር አገልግሎት	16,399,685.40
6	በ2013 ዓ.ም (March, 2021) ለደቡብ ክልል የውሃ፣ መስኖ እና ኢነርጂ ልማት ቢሮ((በውሃና ወሃ ነክ ማሀንዲሶች ማማከር ማህበር)	Consultancy service for water resource potential assessment study in all zones and special woredas found rift vally lakes basin, SNNPRS. የማመከር አገልግሎት	7,135,146.48
7	በ2013 ዓ.ም (dec, 2021) ለደቡብ ክልል ለውሃ፣ መስኖ እና ማዕድን ልማት ቢሮ (በውሃና ወሃ ነክ ማሀንዲሶች ማማከር ማህበር)	consultancy service for water resource potential Assessment study in all zones and special woredas found omo gibe basin, SNNPRS የማማከር አገልግሎቱ	8,556,345
8	በ2014 ዓ.ም ለደቡብ ክልል የመስኖ ተቋማት ልማትና አስተዳደር ኤጀንሲ (በውሃና ወሃ ነክ ማሀንዲሶች ማማከር ማህበር)	የዊንቄ ግድብ መስኖ ፕሮጀክት ጥናት	16,515,392.43
9	በ2013 ዓ.ም ለኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ስራዎች ተቆጣጣሪ ባለስልጣን (በሲቪል ማሃንዲሶች አጠቃላይ የዲዛይን፣ሱፐርቪዥን ማህበር አማከኝነት)	study on cause of corruption in Ethiopia costraction industry and articulate prevention strategy procurement የማማከር አገልግሎት	1,033,000

10	በ2014 ዓ.ም የከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስቴር ለኮንስትራክሽን ማኔጅመንት ኢንስቲትዩት((በሲቪል ማህንዲሶች አጠቃላይ የዲዛይን፣ሱፐርቪዥን ማህበር አማካኝነት)	consultancy service for development of operation manual for Encouraging, promoting and incentivizing bidders introducing new/innovative technologies/adoption during tendering in construction projects የማማከር አገልግሎት	1,500,000

በማማከር አገልግሎት የዊንቂ ግድብ ጥናት የሳይት ሥራ ውሎ አበል ከ15/03/2015 እስከ 04/04/2015 በመስክ ላይ ለቆዩ ሠራተኞች ክፍያ እና የነዳጅ ፍጆታ፤

ሀ. የውሎ አበል ክፍያ

ተ.ቁ	ቦታ	ብዛት	የሎ አበል መጠን	የቆዩበት ቀን	ጠቅላላ
1	ከደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክልል ጉራጌ ዞንና ወረዳ ለመጡ ባለሙያዎች	18	850	18	275,400.00
2	የጥናት ቡድን	5	850	20	85,000.00
	ጠቅላላ ድምር				360,400.00

ለ. የነዳጅ ፍጆታ ክፍያ ለ20 ቀን

መግለጫ	ብዛት	የነዳጅ ፍጆታ ብዛት በሊትር በቀን	የአንድ ሊትር ነዳጅ ዋጋ	ጠቅላላ
የነዳጅ ፍጆታ	2 መኪና	30	61	73,200.00
አጠቃላይ የውሎ አበል እና የነዳጅ ፍጆታ ድምር ሀ+ለ				433,600.00

በማማከር አገልግሎት የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ሰድስት ዞኖች ግድቦች ጥናት ክትትል ቡድን አባላት ውሎ አበል ከ11/04/2015 እስከ 26/04/2015 በመስክ ላይ ለሚቆዩ ሰራተኞች ክፍያ እና የነዳጅ ፍጆታ፤

ሀ. የውሎ አበል ክፍያ

ተ.ቁ	መግለጫ	ብዛት	የሎ አበል መጠን	የቆበዩት ቀን	ጠቅላላ
1	የጥናት ብድኑ አባላት	12	850	16	163,200.00
2	የአስተዳደር	2	850	8	13,600.00
3	ሹፌር	1	850	5	4,250.00
	ጠቅላላ ድምር				181,050.00

ለ. የነዳጅ ፍጆታ

መግለጫ	ብዛት	የነዳጅ ፍጆታ ብዛት በሊትር ለመስክ ስራ እና ለደርሶ መልስ ለአንድ መኪና በቀን	የአንድ ሊትር ነዳጅ ዋጋ	ጠቅላላ
ለነዳጅ	3 መኪና	365	61	66,795.00
አጠቃላይ የውሎ አበል እና የነዳጅ ድምር ሀ+ለ				247,845.00

የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ስድስት ዞኖች ግድቦች የሶስተኛ ዙር የዊንቄ ግድብ ጥናት ክትትል ቡድን አባላት ውሎ አበል ከ13/05/2015 እስከ 30/05/2015 በመስክ ላይ ለሚቆዩ ተሳታፊዎች የውሎ አበል እና የነዳጅ ፍጆታ ክፍያ፤

ሀ. የውሎ አበል ክፍያ

ተ.ቁ	መግለጫ	ብዛት	የሎ አበል መጠን	የቆዩበት ቀን	ጠቅላላ
1	የጥናት ብድኑ አባላት	10	850	18	153,000.00
2	ከደቡብ መዕ/ኢ.ት/ሕዝቦች ክልል መስኖ ኤጀንሲእና አጋር ቢሮዎች የሚሳተፉ	8	850	14	95,200.00
3	ከኢንተርፕራዙ ለሚሳተፉ	3	850	8	20,400.00
	ጠቅላላ ድምር				268,600.00

ለ. የነዳጅ ፍጆታ (ለ18 ቀናት)

መግለጫ	ብዛት	የነዳጅ ፍጆታ ብዛት በሊትር ለደርሶ መልስ ለአንድ መኪና በቀን	የአንድ ሊትር ነዳጅ ዋጋ	ጠቅላላ
ለነዳጅ	2 መኪና	35	70	88,200.00
አጠቃላይ የውሎ አበል እና የነዳጅ ድምር ሀ+ለ				268,600.00

በማማከር አገልግሎት ስራ ላይ አስተዋጽኦ ላበረከቱ ባለሙያዎች እና የአስተዳደር ሰራተኞች የጉርሻ ክፍያ

የኦሞ-ጊቤ ተፋሰስ ላይ የውሃ አቅም እና ነባር የመጠጥ ውሃ ተቋማት ያሉበትን ደረጃ ለማጥናት ለተሳተፉ ባለሙያዎች እና የአስተዳደር ሰራተኞች ቦነስ ክፍያ፡-

በማማከር አገልግሎት ላይ ለተሳተፉ ባለሙያዎች				
ተ.ቁ	ስም	አጠቃላይ ቦነስ ክፍያ	ዊዝሆልዲንግ 30%	የተጣራ ክፍያ
1	ዶክተር ሞልቶ ዘውዴ	269,507.95	80,852.39	188,655.57
2	ዶክተር አለማየሁ ሙሉነህ	269,507.95	80,852.39	188,655.57
3	አቶ አየለ ጌታቸው	269,507.95	80,852.39	188,655.57
4	አቶ አወል ሰይድ	160,000.	48,000.00	112,000.00
	ድምር	968,523.85	290,557.14	677,966.70
ለአስተዳደር ሰራተኞች ላበረከቱት አስተዋጽኦ የተከፈለ ቦነስ				
5	አጠቃላይ ድምር	46,550		

አባሪ 4፡- በዝርዝር ኦዲት ወቅት የተከለሱ መረጃዎች

1. የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት አዋጅ ቁጥር 650/2001
2. የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት አዋጅ ቁጥር 1152/2011
3. የመንግስት ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የገቢ ማስገኛ ድርጅት ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 456/2012
4. የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የገቢ ማስገኛ ድርጅቶች የሚተዳደሩበትን ሥርዓት ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 04/2012
5. የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የውስጥ ገቢ መመሪያ ቁጥር 39/2006
6. የፌዴራል መንግስት የውስጥ ቁጥጥር ደረጃዎች መመሪያ ቁጥር 8/2003)
7. የፌደራል መንግስት የጥሬ ገንዘብ አስተዳደር መመሪያ 3/2003
8. በመንግስት በጀት ለሚሸፈኑ ወጪዎች የክፍያ መመሪያ ቁጥር 913/2014
9. የመንግስት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁር /25/84
10. የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ የገቢ ማመንጫ ኢንተርፕራይዝ የመመስረቻ ፅሁፍ እና መተዳደሪያ ደንብ
11. የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ የገቢ ማመንጫ ኢንተርፕራይዝ የቦርድ ቃለ-ጉባኤ
12. የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ የገቢ ማመንጫ ኢንተርፕራይዝ የማኔጅመንት ቃለ-ጉባኤ
13. የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ የገቢ ማመንጫ ኢንተርፕራይዝ ከ 2011 ዓ.ም እስከ 2014 ዓ.ም ያሉ እቅድ እና የእቅድ አፈፃፀም ሪፖርቶች
14. የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ገቢ ማመንጫ ኢንተርፕራይዝ የአሰራር ማኗሎች እና መመሪያዎች

አባሪ፡ 5 በኦዲት ወቅት በናሙና ተመርጠው የታዩ የኢንተርፕራይዙ ማዕከላት እና የዩኒቨርስቲው ኮሌጆች

1. የኢንተርፕራይዙ ዕርሻ ማዕከል
2. የኢንተርፕራይዙ የሆቴል አገልግሎት ማዕከል
3. በኢንተርፕራይዙ የግብርና ኮሌጅ የእንጨትና ብረታብረት ዕደ-ጥበብ ማዕከል
4. በኢንተርፕራይዙ በወንዶ ገነት ደንና ተፈጥሮ ሀብት ኮሌጅ የእንጨትና ብረታብረት ዕደ-ጥበብ ማዕከ
5. የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ዋናው ግቢ
6. በሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ የተክኖሎጂ ኢንስቲትዩት
7. የግብርና ኮሌጅ
8. የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ጤና ሳይንስ ኮሌጅ
9. በሀዋሳ ዩኒቨርስቲ የወንዶ ገነት ደንና ተፈጥሮ ሀብት ኮሌጅ